# ❖ የያዕቆብ

# ❖ 1ኛ፤ 2ኛና 3ኛ የዮሐንስ
# እና
# ❖ የይሁዳ መልዕክቶች

በመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት አገልግሎት ቡድን የተዘጋጀ

<u>ሴፕቴምበር 2021</u>

# በመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት አገልግሎት ቡድን የተዘጋጀ

ሴፕቴምበር 2021

## ማውጫ


አርዕስት ገጽ

ክፍል አንድ ........ 2

1.የያዕቆብ መልዕክት መግቢያ ........ 3

ጥናት 1: መከራና ፈተና, ........ 5

ጥናት 2: መስማትና ማድረግ ........ 6

ጥናት 3: ከአድሎአዊነት መጽዳት ........ 7

ጥናት 4: እምነትና ሥራ ........ 8

ጥናት 5: አንደበትን መግታት ........ 9

ጥናት 6: የጥበብ ምንጮች ........ 10

ጥናት 7: ለእግዚአብሔር መገዛት........ 11

ጥናት 8: ስለ ነገ መመካት........ 12

ጥናት 9: ለጨቋኝ ባለጠጎች ማስጠንቀቂያ ........ 13

ጥናት 10: በመከራ መታገስ ........ 14

ጥናት 11: የእምነት ፀሎት........ 15

ክፍል ሁለት: 1ኛው፤ 2ኛው እና 3ውኛ የዮሐንስ መልዕክቶች........ 16

2.1. የሐዋርያው ዮሐንስ መልዕክት - አንደኛ መግቢያ ........ 17

ጥናት 1: በብርሃን መመላለስ........ 20

ጥናት 2: የመታዘዝ ሕይወት........ 21

ጥናት 3: ክክርስቶስ ተቃዋሚዎች መጠንቀቅ ........ 22

ጥናት 4: የአማኞች ፍቅር ........ 23

ጥናት 5: መንፈስን መርምሩ........ 24

ጥናት 6: በክርስቶስ ማመን ........ 25

ጥናት 7: የማጠቃለያ ምክር ........ 26

2.2 የሐዋርያው ዮሐንስ መልዕክት - ሁለተኛ መግቢያ........ 27

ጥናት 8: ሽማግሌው........ 28

2.3 የሐዋርያው ዮሐንስ መልዕክት - ሦስተኛ መግቢያ........ 29

ጥናት 9: ሽማግሌው ........ 30

ክፍል ሦስት: የያዕቆብ ወንድም የይሁዳ መልዕክት........ 31

የይሁዳ መልዕክት- መግቢያ........ 32

ጥናት 1: ዐመጻኞች የሚጠብቃቸው ፍርድ........ 33

ጥናት 2: በእምነት መጽናት ........ 34

# ክፍል አንድ

## <u>የያዕቆብ መልዕክት</u>

<u>**የያዕቆብ መልዕክት**</u>

## መግቢያ

**ፀሐፊው:-ያዕቆብ**

በአዲስ ኪዳን ውስጥ በያዕቆብ ስም የተጠሩ ከአራት በላይ ሰዎችን እናገኛለን ። ለዚህ የጥናት ዝግጅት እንዲረዳን የሚከተሉትን ሁለቱን ብቻ በጥቂቱ እንመልከት:

**አንደኛው** ከአስራ ሁለቱ ደቀ መዛሙርት (ወይንም የበጉ ሐዋርያት) አንዱ የሆነው የዘብዴዎስ ልጅ የዩሐንስ ወንድም ሐዋርያው ያዕቆብ ነው(ማቴ 4፥21) ። ሐዋርያው ያዕቆብ በ44 ዓ.ም ሰማዕት ስለሆነ የያዕቆብ መልዕክት ደግሞ የተጻፈው ከ58-60 ዓ.ም ነው ። ስለዚህ ሐዋርያው ያዕቆብ ሊሆን አይችልም ምክንያቱም በህይወት አልነበረም ።

**ሁለተኛው** ደግሞ የማርያም እና የዮሴፍ ልጅ የኢየሱስ ክርስቶስ ወንድም (ማቴ13:55) የተገለጸው የአስቆሮቱ ይሁዳ ያልሆነው የይሁዳ ወንድም ያዕቆብ ነው ። ምንም እንኳ ያዕቆብ የክርስቶስን መለኮትነት ለመቀበል ጊዜ ቢወስድበትምቆይቶ ግን በቤተክርስቲያን ዋና (አዕማድ) ተብለው ከተጠሩት ውስጥ አንዱ ብቻ ሳይሆን የያዕቆብ መልዕክት ፀሓፊ መሆኑን "የእግዚአብሔርና የጌታ የኢየሱስ ክርስቶስ ባሪያ ያዕቆብ" በማለት በምዕራፍ 1:1 ላይ ገልጿል ።

## ተደራስያኑ

የመጀመርያው ተደራስያን ሰዎች አይሁዶች ለመሆናቸው ምንም ጥርጥር የለውም ። ምክንያቱም በምዕራፍ 1:1 ላይ "ለተበተኑ ለአሥራ ሁለቱ ወገኖች" ይላል የተበተኑ አሥራ ሁለቱ ወገኖች ደግሞ አይሁዶች ናቸው ከዚህ በተጨማሪ ፀሓፊው አይሁዳዊ መሆኑእና በእነርሱ ዘንድ የተለመደ "ወደ ጌታ ፀባዖት" 5:4 የሚለውን ቃል መጠቀሙ የበለጠ አርግጠኛ እንድንሆን ያደርገናል ።

## ታሪካዊ ዳራ

የተፃፈላቸው ሰዎች በቅርበት የሚያውቃቸው መሆኑን ከሚጠቁመን ነገር አንዱ በአምስት ምዕራፍ ውስጥ ብቻ አስራአምስት ጊዜ ወንድሞቼ እያለ ጠርቶአቸዋል ። የመበተናቸው ዋና ምክንያት ነው ተብሎ የሚታወቀው ግን ሐዋርያት ስራ ምዕራፍ ሰባት የእስጢፋኖስን በድንጋይ መወገር አስመልክቶ ምዕራፍ ስምንት ላይ በኢየሩሳሌም ባለች ቤተ ክርስቲያን ያዕቆብ በዋና መሪነት በሚያስተዳድራት ቤተክርስቲያን ላይ ታላቅ ስደት መነሳቱና ከሐዋርያት በቀር ወደ ይሁዳና ወደ ሰማርያ አገሮች መበተናቸው እንዲሁም ሐዋርያት ሥራ 11:19 በእስጢፋኖስም ላይ በተደረገው መከራ የተበተኑት እስከ ፊንቄ እስከ ቆጵሮስም እስከ አንጾኪያም ድረስ መዞራቸውን በግልፅ ተቀምጦልናል ። ከዚህ ታሪካዊ ዳራ በመነሳት ያዕቆብ ያውቃቸው ለነበሩ አሁን ግን ለተበተኑ ክርስቲያን አይሁዶች የተፃፈ ነው ።

## የተጻፈበት ዓላማ

ከመጀመሪያዪቱ የጴጥሮስ መልዕክት ጋር ተመሳሳይነት ያለው የያዕቆብ መልዕክት ክርስትናን እንዴት መኖር እንዳለብን አበክሮ ይመክረናል ። በአጭር ቃል የምክር መልእክት ነው ቢባል ማጋነን አይሆንም ። በዚህ ክፍል ክርስቶስ ኢየሱስ በነገር ሁሉ በጽድቅ እየተመላለሰ ብዙ መከራ እንደደረሰበት ሁሉ አማኝም ጌታውን ሊመስል በወደደ መጠን በሕይወቱ ፈተና ሊገጥመው እንደሚችል ያስገነዝባል ። በመቀጠልም ቃሉን ሰምቶ የሚያደርግ የተግባር ሰው እንድንሆንና በሌሎችም መሃል አድሎአዊነትን እንዳናሳይ ይመክራል ። አንደበት ትንሽ የአካል ክፍል ቢሆንም ካልተገራ ግን ከሰዎች ጋር በሚኖር ግንኙነት ጉዳት ሊያደርስ እንደሚችል ያስጠነቅቃል ። ባለጠጎች ሀብታቸውን በአግባቡ እንዲጠቀሙበት ይመክራል ። በክርስቶስ በማመን የጸደቀ ሰው እምነቱን በስራ መግለጥ እንደሚጠበቅበትም ያስተምራል ። ጽናትና የጻድቅ ሰው ጸሎት ሊያመጡ የሚችሉት ፍሬዎች በመልዕክቱ የተካተቱ እውነቶች ናቸው ።

በመሆኑም ያዕቆብ መልዕክት ሲጽፍ ዋና ዓላማው:

1. እምነታቸውን የሚፈትን የተለያየ መከራ የደረሰባቸውን ከአይሁድ ወገን ወደ ጌታ የመጡትን አማኞች ማጽናናትና ማበረታታት
2. የሚያድን እምነት ባሕርይ ምን እንደሆነ በሚገባ ካለመረዳት የተነሳ የተከሰተውን የተሳሳተ ሐሳብ ማረም
3. መልዕክቱን ተቀብለው የሚያነቡ ሰዎች በጽድቅ በመኖርና መልካም የሆነውን ነገር በማድረግ እምነታቸውን በስራ እንዲገልጡ አጥብቆ መምከርና ማስተማር ናቸው ።

## ጥናት 1
## መከራና ፈተና
## <u>የምንባብ ክፍል : ያዕ 1:1-18</u>

**መግቢያ:-** በዛሬው የመጀመሪያ ጥናታችን አማኞች በማንኛውም መከራና ፈተና ውስጥ ሲያልፉ እንዴት መጽናት እንዳለባቸውና እግዚአብሔርም በክፉ እንደማይፈትን እንመለከታለን ።

**የመወያያ ጥያቄዎች**

1. /ከቁ.2-4/ የእምነታችን መፈተን ትዕግስት ሊያስገኝልን እንዴት እንደሚችል አብራሩ ። በተጨማሪ 1ጴጥ1:7ን ያንብቡ።
2. /ከቁ.5-6 /"ከእናንተ ግን ማንም ጥበብ ቢጎድለው፥ ሳይነቅፍ በልግስና ለሁሉ የሚሰጠውን እግዚአብሔርን ይለምን፥ ለእርሱም ይሰጠዋል" ይላል ። ጥበብ እንደጎደለን እንዴት ማወቅ እንችላለን?
3. /ከቁ.7-12/ እግዚአብሔርን እንደ ቃሉን ከማመን ይልቅ መጠራጠር በሕይወታችን ምን ሊያስከትል እንደሚችልና የሕይወትን አክሊል የሚቀበል ሰው ደግሞ ምን አይነት ሰው  እንደሆነ አብራሩ ።
4. /ከቁ.13-15/ እግዚአብሔር በክፉ የማይፈትን ከሆነ ይህን የመሰለ ፈተና ወደ ሕይወታችን በምን ምክንያት ሊመጣ እንደሚችል ተወያዩ ።
5. /ከቁ.16-18/ "ለፍጥረቱ የበኵራት ዓይነት እንድንሆን በእውነት ቃል አስቦ ወለደን" ሲል ምን ማለቱ እንደሆነ ከአውዱ በመነሳት ተወያዩበት ።

**ከሕይወት ጋር ማዛመድ**

6. የሰው ልጆች ሁሉ በልዩ ልዩ መከራና ፈተናዎች የሚያልፉ ቢሆንም የክርስቶስ ተከታዮች የሚያልፉበት መከራና የሚገጥምቸው ፈተና ከሌሎቹ  በምን ሊለይ እንደሚችል የሕይወት ተሞክሮአችሁን አጋሩ ።

❖ **በዛሬው ምንባብ በመወያያ ጥያቄዎቹ ያልተዳሰሰ  ሀሳብ ካለ በቀራችሁ ጊዜ ተወያዩበት ።**

**ማጠቃለያ**

 እንደ አማኝ በልዩ ልዩ መከራ ውስጥ ስናልፍ በእምነታችን መጽናት እንዳለብን ፣ በሕይወታችን የእግዚአብሔርን ጥበብ መለመን እንደሚገባን ፣ እግዚአብሔር በክፉ እንደማይፈተን ሁሉ እኛንም እንደማይፈትን ነገር ግን ከገዛ ስጋዊ ምኞቶቻችን የተነሳ በክፉ ልንፈተን እንደምንችል እና በመጨረሻም የበጎ ስጦታና የፍጹም በረከት ምንጭ የሆነው ጌታ የፍጥረቱ በኩራት እንድንሆን በእውነት ቃል አስቦ እንደወለደን ተመልክተናል ።

**በቃል የሚጠና**

"ማንም ሲፈተን ። በእግዚአብሔር እፈተናለሁ አይበል፤ እግዚአብሔር በክፉ አይፈተንምና፤ እርሱ ራሱስ ማንንም አይፈትንም" **ያዕ 1:13**

**ጥናት 2**

**መስማትና ማድረግ**

**<u>የምንባብ ክፍል: ያዕ 1:19-27</u>**

**መግቢያ:-** ባለፈው ጥናት እንደ አማኝ በልዩ ልዩ መከራ ውስጥ ስናልፍ በእምነታችን መጽናት እንዳለብን ፣ በሕይወታችን የእግዚአብሔርን ጥበብ መለመን እንደሚገባን ፣ እግዚአብሔር በክፉ እንደማይፈተንና እኛንም እንደማይፈትን ነገር ግን ከገዛ ስጋዊ ምኞቶቻችን የተነሳ በክፉ ልንፈተን እንደምንችል እና በመጨረሻም የበጎ ስጦታና የፍጹም በረከት ምንጭ የሆነው ጌታ የፍጥረቱ በኩራት እንድንሆን በእውነት ቃል አስቦ እንደወለደን ተመልክተን ነበር ። በዛሬው ጥናታችን ደግሞ ማንኛውም ክርስቲያን የእግዚአብሔር ቃል ሰሚ ብቻ ሳይሆን የሰማውን ቃል ታዞ በሕይወቱ እየተገበረ መኖር እንደሚጠበቅበት በዝርዝር እንመለከታለን ።

**የመወያያ ጥያቄዎች**

1. በቁ. 19 ላይ ያዕቆብ "ሰው ሁሉ ለመስማት የፈጠነ ለመናገር ግን የዘገየ ይሁን" ብሎ የሚመክረው ለምን ይመስላችኋል?
2. /ከቁ.20-21/ ያዕቆብ "የሰው ቁጣ የእግዚአብሔርን ጽድቅ አይሰራም" ሲል ምን ማለቱ እንደሆነና ከዚያ ይልቅ ምን ማድረግ እንደሚባ የመከራቸውን አብራሩ ።
3. /ከቁ.22-25/ ቃሉን ሰምቶ የማያደርግ ሰው ራሱን እንሚያስትና ፊቱን በመስታወት አይቶ ወዲያው እንደሚረሳ ሰው ነው ያለበት ምክንያት ለምን ይመስላችኋል ?ቃሉን በስራ የመግለጥ ጠቀሜታው ምንድር ነው ?
4. በቁ.26 ላይ ያዕቆብ "አንደበቱን ሳይገታ ልቡን እያሳተ እግዚአብሔርን የሚያመልክ የሚመስለው ማንም ቢኖር የእርሱ አምልኮ ከንቱ ነው" ሲል ምን ማለቱ ነው ?
5. በቁ.27 ላይ በእግዚአብሔር ፊት ንጹሕ የሆነ ነውርም የሌለበት አምልኮ ተብሎ የተጠቀሰው ተግባር ምን ምንድር ነው?

## ከሕይወት ጋር ማዛመድ

6. **የእግዚአብሔርን ቃል ሰምተን መታዘዛችን በየዕለቱ የሕይወት እርምጃችን በተግባር እንዴት ሊገለጥ እንደሚችል ተሞክሮአችሁን አጋሩ ።**

❖ **በዛሬው ምንባብ በመወያያ ጥያቄዎቹ ያልተዳሰሰ ሀሳብ ካለ በቀራችሁ ጊዜ ተወያዩበት ።**

**ማጠቃለያ**

በምንባባችን ለመዳሰስ እንደሞከርነው ቃሉን መስማት አስፈላጊ የመሆኑን ያህል ከመስማት ባለፈ ግን በተግባር መታዘዝና በዕለታዊ ኑሮ እንዴት በሕይወታችን ልንገልጠው እንደሚገባ ያዕቆብ የተለያዩ ማሳያዎችን በመጥቀስ እግዚአብሔርን በእውነት ልናመልከው እንደሚገባን በአፅንዖት ይመክራል ።

**በቃል የሚጠና**

"ቃሉን የምታደርጉ ሁኑ እንጂ ራሳችሁን እያሳታችሁ የምትሰሙ ብቻ አትሁኑ" **ያዕ1:2**

## ጥናት 3

## ከአድሎአዊነት መጽዳት

## <u>የምንባብ ክፍል : ያዕ 2:1-13</u>

**መግቢያ:-**ባለፈው ጥናት ቃሉን መስማት አስፈላጊ የመሆኑን ያህል ከመስማት ባለፈ ግን በተግባር መታዘዝና በዕለታዊ ኑሮ እንዴት በሕይወታችን ልንገልጠው እንደሚገባ ያዕቆብ የተለያዩ ማሳያዎችን በመጥቀስ እግዚአብሔርን በእውነት ልናመልከው እንደሚገባን በአፅንዖት የመከረበትን ክፍል ተመልክተን ነበር ። በዛሬ ጥናታችን ደግሞ አማኝ ሰዎችን በሰውነታቸው እኩል እንድናይ እንጂ በለተያዩ መስፈርቶች ለሰዎች ደረጃ በመስጠት አድልዎ መፈጸም በእግዚአብሔር ዘንድ የሚያስነቅፍ መሆኑንና ከአድሎአዊነት ሕይወት እንድንጠበቅ ያዕቆብ የመከረበትን እውነቶች በዝርዝር እናያለን ።

### የመወያያ ጥያቄዎች

1. /ከቁ 1-4/ያዕቆብ አድልዎ እንዳታደርጉ ብሎ የጠቀሳቸውን ሰዎችን መፈረጃ ነጥቦች በመዘርዘር አድልዎ የሚያደርጉ አማኞች በምን የተያዙ ሊሆኑ እንደሚችሉ ግለጹ ።
2. /ከቁ 5-7/ እግዚአብሔር ለድሆች የሰጠው ስፍራ እስከየት እንደሆነና ያዕቆብ እየመከራቸው የነበሩት ወገኖች ድሆችን ምን እንዳደረጓቸው በዝርዝር ተወያዩ ።
3. በቁ 8. ላይ “ባልንጀራህን እንደ ራስህ ውደድ” የሚለው ትዕዛዝ ምን ማለት እንደሆነ በማብራራት ” የንጉስ ሕግ ትፈጽማላችሁ” የተባለው ‘ንጉስ’ ማን ይመስላችኋል ? / ለማመሳከሪያ ማቴ22:34-40/ ያንብቡ ።
4. በቁ. 9 ላይ ሕግ ተላላፊ ተደርገው የሚወቀሱት ሰዎች ምን ዓይነት ኃጢአት የሚፈጽሙ ሰዎች ናቸው?
5. /ከቁ 10-11/ ሕግን ሁሉ የሚፈጽም ነግር ግን አንዱን ቢያጎድል ሁሉን እንደተላለፈ እንደሚቆጠር ይናገራል ። ለመሆኑ ሰው አንዳች ሳያጎድል ሕግን ሁሉ ሊጠብቅ የሚቻለው ይመስላችኋል ? እንዴት?
6. ከቁ./12-13/ ያለውን በማንበብ ” ምሕረትን ለማያደርግ ምሕረት የሌለበት ፍርድ ይሆናልና፤ ምሕረትም በፍርድ ላይ ይመካል” የሚለው ቃል ምን ማለት እንደሆነ ተወያዩ ።

### ከሕይወት ጋር ማዛመድ

7. በዘመናችሁ እናንተ ላይ አድልዎ ተፈጽሞባችሁ ያውቃል ?/ የሰዎችን ስም አትጥቀሱ/ መልሳችሁ አዎ ከሆነ ምን ተሰማችሁ? እናንተስ በሌሎች ላይ አድልዎ ፈጽማችሁ ታውቃላችሁ? በታማኝነት ተሞክሮአችሁን አጋሩ ።

- **በዛሬው ምንባብ በመወያያ ጥያቄዎቹ ያልተዳሰሰ ሀሳብ ካለ በቀራችሁ ጊዜ ተወያዩበት ።**

### ማጠቃለያ

“ባልንጀራህን እንደ ራስህ ውደድ” እንደሚለው ወርቃማ የጌታ ትዕዛዝ እኛም ለማንም ፊት ሳናደላ እንደ እውነተኛ የክርስቶስ ተከታይ ሰዎችን ሁሉ በእኩል ዓይን ተመልክተን እንድንወዳቸው፣ይቅርታ እንድናደርግላቸው ፣ እንድናከብራቸውና እንድናገለግላቸው በመምከር ከአድልዎአዊነት እንድንጠበቅ የእግዚአብሔር ቃል ያስተምረናል።

### በቃል የሚጠና ጥቅስ

“ለሰው ፊት ግን ብታደሉ ኃጢአትን ትሠራላችሁ፥ ሕግም እንደ ተላላፊዎች ይወቅሳችኋል።” **ያዕ2:9**

## ጥናት 4
## እምነትና ሥራ
**የምንባብ ክፍል: ያዕ 2:14-26**

**መግቢያ:** ባለፈው ጥናት ከአድሎአዊነት እንድንጠበቅ ለማንም ፊት ሳናደላ እንደ እውነተኛ የክርስቶስ ተከታይ ሰዎችን ሁሉ በእኩል ዓይን እንድንወዳቸው፣ይቅርታ እንድናደርግላቸው ፣ እንድናከብራቸውና እንድናገለግላቸው ያዕቆብ የመከረበትን እውነት ተመልክተን ነበር ። በዛሬው ጥናታችን ደግሞ "ሥራ የሌለው እምነት ቢኖር የሞተ ነው" በማለት እምነትና ሥራ የማይነጣጠሉ የአማኝ ወይም የመንፈሳዊ ሰው የሕይወት ገጽታዎች መሆናቸውን የመከረበትን በዝርዝር እንዳስሳለን ። እምነት እንዴት በስራ ማሳየት እንዳለብን እናያለን ።

**የመወያያ ጥያቄዎች**

1. በቁ.14 ላይ እምነት አለኝ የሚል ሰው ተግባራዊ የእምነት ሥራ በሕይወቱ ካልተንጸባረቀበት እምነት አለኝ ማለቱ ብቻ በራሱ ምን ሊጠቅመው ይችላል?
2. /ከቁ.15-16/ አንድ ሰው የሚያድን እምነት ያለው ስለመሆኑ በሕይወቱ ሊገልጥባቸው ከሚችሉ ጠቃሚ ምሳሌነቶች በመጥቀስ ተወያዩ ።
3. /ከቁ.17-18/ ያለውን በማንበብ "ሥራ የሌለው እምነት ቢኖር የሞተ ነው" ሲል መዳን በስራ ነው ማለቱ ነው? ካልሆነስ? ምን ማለት እንደሆነ በጥልቀት ተነጋገሩ ።
4. በቁ.19 ላይ እግዚአብሔር አንድ አንደሆነ አማኝ ሰው እንደሚያምን ሁሉ አጋንንትም ይህንኑ ስለሚያምኑ የሁለቱን የእምነት ልዩነት አብራሩ።/ለተጨማሪ ማብራሪያ ማር5:1-9 ያለውን ይመልከቱ/
5. /ከቁ.20-25/ያለውን በማንበብ አባታችን አብርሃም እንዲሁም ጋለሞታይቱ ረዓብ የፈጸሙትን እንደ ጽድቅ ያስቆጠረላቸውን የእምነትነት ሥራ በዝርዝር ተወያዩ ።

**ከሕይወት ጋር ማዛመድ**

6. እኛ ክርስቶስ በሰራው ስራ ብቻ በእምነት የዳንን ብንሆንም ነገር ግን በቁ.26 ላይ "ከነፍስ የተለየ ሥጋ የሞተ እንደ ሆነ እንዲሁ ደግሞ ከሥራ የተለየ እምነት የሞተ ነው" እንደሚለው በፍሬ የሚገለጥ ተግባራዊ የክርስትና ሕይወት የሚጠበቅብን ለምንድር እንደሆነ ለቡድናችሁ አጋሩ ።

- **በዛሬው ምንባብ በመወያያ ጥያቄዎቹ ያልተዳሰሰ ሀሳብ ካለ በቀራችሁ ጊዜ ተወያዩበት ።**

**ማጠቃለያ**

ዛሬ በተመከትነው ምንባብ ያዕቆብ ለድነት የሚያበቁን እምነትና ስራ ናቸው ማለቱ ሳይሆን በስራ ስለሚገለጽ እምነት ነው ። ይህም ማለት ክርስቶስ በሰራው ስራ ብቻ የጸደቀ ሰው ከእምነቱ የመነጨ ተግራራዊ አኗኗር በሕይወቱ ሊገለጥበት ይገባል ለማለት ነው ። ስለዚህ ያዕቆብ ብዙ ምሳሌዎችን ጠቅሶ እንዳስረዳን እምነትና ሥራ የማይነጣጠሉ የአማኝ ወይም የመንፈሳዊ ሰው የሕይወት ገጽታዎች ናቸው ማለት ይቻላል ። በመሆኑም እኛም በክርስቶስ የመስቀል ሥራ ብቻ አምነን የዳንን ሰዎች አንዴ ከዳንን በኋላ ዳግም በሥራ ለመጽደቅ ብለን ሳይሆን ከዳነ ሰው የሚጠበቅብንን ክርስቲያናዊ አኗኗርን በሚመጥን ደረጃ በመኖር እምነታችንን በሥራ ልንገልጥ ይገባናል ።

**በቃል የሚጠና**

"ከነፍስ የተለየ ሥጋ የሞተ እንደ ሆነ እንዲሁ ደግሞ ከሥራ የተለየ እምነት የሞተ ነው" **ያዕ 2:26**

## ጥናት 5
## አንደበትን መግታት
## <u>የምንባብ ክፍል: ያዕ 3:1-12</u>

**መግቢያ:** ባለፈው ጥናት ያዕቆብ "ሥራ የሌለው እምነት ቢኖር የሞተ ነው"በማለት እምነትና ሥራ የማይነጣጠሉ የአማኝ ወይም የመንፈሳዊ ሰው የሕይወት ገጽታዎች መሆናቸውን የመከረበትን እውነት በመዳሰስ እንዴት እምነታችንን በስራ መግለጽ እንዳለብን ተመልክተን ነበር ። በዛሬው ጥናታችን ደግሞ አንደበት ትንሽ ብልት ቢሆንም ከአንደበት አለመገታት የተነሳ በንግግራችን ሂደት ኃጢአት የመፈጸም ዝንባሌ እንደሚኖር በመግለጽ ሊደርስ የሚችለውን ጉዳት ለመከላከል አንደበታችን በቃሉ መገራት እንደሚገባው የመከረበትን እውነታዎች እንቃኛለን ።

**የመወያያ ጥያቄዎች**

1. ከቁ.1-2 እንደተገለጸው "አስተማሪዎች" ማለት ምን አይነት አገልጋዮች የሚያካትት ይመስላችኋል? የባሰ ፍርድ የሚቀበሉትስ ለምንድር ነው?
2. /ከቁ.3-5/ አንደበት አንስተኛ የአካል ክፍል ሆኖ ሳለ ነገር ግን መላ ስብዕናን በአደገኛ ሁኔታ ሊዘውር እንደሚችል ያዕቆብ ለማብራራት የተጠቀመባቸውን ምሳሌዎች በመዘርዘር ተነጋገሩ ።
3. በቁ.6 ላይ "አንደበትም እሳት፤ ዓመፀኛ ዓለም፤ ሥጋን ሁሉ ያሳድፋል፥ የፍጥረትንም ሩጫ ያቃጥላል፥ በገሃነምም ይቃጠላል።" በሚሉ ሐረጎች ተገልጿል። አንደበታችን ይህን ሁሉ የማድረግ አቅም እንዴት ሊኖረው እንደሚችል በመተንተን ተወያዩ ።
4. /ከቁ.7-8/ የሰው ልጅ የቤት እንስሳትን ብቻ ሳይሆን የዱር አራዊትን እንኳን መግራት እየቻለ ነገር ግን የገዛ አንደበቱን መግራት አለመቻሉ መርዝ የሞላበት እረፍት የለሽ ክፉ ነገር ናት ይለዋል ። ይህ ከሆነ ታዲያ ሰው አንደበቱን መግታት እንዴት መለማመድ የሚችል ይመስላችኋል?
5. /ከቁ .9-12/ በአንደበታችን ከሚወጣው በረከትና መርገም በመነሳት ያዕቆብ"ወንድሞቼ ሆይ፥ ይህ እንዲህ ሊሆን አይገባም" ብሎ የቃላቶቻችን ምንጮች እንድንፈትሽ የጠቀሳቸውን ምሳሌዎች በመተንተን ተወያዩ ።

**ከሕይወት ጋር ማዛመድ**

6. አንደበትን ለመግታት፤ የንግግርን ችሎታን ለማሻሻል ፤ የሌሎችን ሰብዓዊ ክብርና ጎሊና ጠብቆ የራስን ሐሳብን ባግባቡ ለመግለጽ፤ ባጠቃላይ ከሰዎች ጋር የሚኖረንን ጤናማ ተግባቦት ለማበልጸግ ምን ማድረግ ይጠበቅብናል ?

- **በዛሬው ምንባብ በመወያያ ጥያቄዎቹ ያልተዳሰሰ ሀሳብ ካለ በቀራችሁ ጊዜ ተወያዩበት ።**

**ማጠቃለያ**

የአንደበታችንን አዎንታዊም ይሁን አሉታዊ ሚና በመረዳት ከሰው ሁሉ ጋር በሰላምና በፍቅር እንድንኖር አንደበታችንን ለመግራት የሚያስችለንን ቅዱሳት መጽሐፍትን ማንበብ፤ ጥበብን በጸሎት መጠየቅ ፤ ራስን መግዛት፤በማስተዋል መናገር፤ ሌላውን ሰው ከራስ እንደሚሻል በትህትና በመቁጠር ማክበርና በአጭሩ ክርስቶስን መምሰልን በማስለመድ ራሳችንን ማሰልጠን ይገባናል ።

**በቃል የሚጠና**

"አንደበቱን ሳይገታ ልቡን እያሳተ እግዚአብሔርን የሚያመልክ የሚመስለው ማንም ቢኖር የእርሱ አምልኮ ከንቱ ነው"

**ያዕ1:26**

## ጥናት 6
## የጥበብ ምንጮች
## <u>የምንባብ ክፍል: ያዕ 3:13 -18</u>

**መግቢያ:-**ባለፈው ጥናት ደግሞ አንደበት ትንሽ ብልት ቢሆንም ከአንደበት አለመገታት የተነሳ በንግግራችን ሂደት ኃጢአት የመፈጸም ዝንባሌ እንደሚኖር በመግለጽ ሊደርስ የሚችለውን ጉዳት ለመከላከል አንደበታችን በቃሉ መገራት እንደሚገባው የመከረበትን እውነታዎች ተመልክተን ነበር ። በዛሬው ጥናታችን ደግሞ ምንጫቸው የተለያዩ የሆኑ ከላይ የሚወርድ ፤ የምድር ነው፥ የሥጋም ነው፥ የአጋንንትም ነው ተብለው የተጠቀሱ የጥበብ ዓይነቶችን ምን እንደሚመስሉ በዝርዝር እናያለን ።

### የመወያያ ጥያቄዎች

1. በቁ.13 ላይ የተጠየቀው የጥበበኛና የአስተዋይ ሰው መለኪያው ምንድር ነው?
2. አስተዋይ ሰው ሥራውን ከጥበብ በሆነ መልካም አኗኗር ማሳየት እንዴት የሚችል ይመስላችኋል?
3. በቁ.14 ላይ እንደተጠቀሰው እውነትን የሚክዱ ሰዎች በልባቸው ምን ዓይነት ባሕርይ ተሸክመው እንደሚኖሩ በመዘርዘር ተወያዩ ።
4. ከቁ.15-16 እንደተገለጹት ምንጫቸው <u>**ምድራዊ፤ ሥጋዊና አጋንንታዊ**</u> የሆኑ የጥበብ ዓይነቶች ምን ምን የመሰሰሉ ናቸው? እንዲህ ዓይነት ጥበብ በሞላበት ሥፍራ ሊገኝ የሚችለው ውጤትስ ምን ይመስላችኋል?
5. ከቁ.17-18 ምንጫቸው <u>**ላይኛቱ/ ከሰማይ**</u> ተብለው የተገለጹት የጥበብ ባሕርያት ምን ምን የመሰሰሉ ናቸው? እንዲህ ዓይነት ጥበብ በሞላበት ሥፍራ ሊገኝ የሚችለው ውጤት ምን እንደሆነ በዝርዝር ተወያዩ ።

### ከሕይወት ጋር ማዛመድ

6. እኛ በዚህ ዘመን የምንገኝ አማኞች ምድራዊ ፤ ሥጋዊና አጋንታዊ ጥበብ ተብለው ከተዘረዘሩት ቅንዓት፤ መራርነት፤ ራስ ወዳድነት ፤ አድመኝነትና ወ.ዘ.ተ ከመሳሰሉት ባሕርያት ውስጣችን ምን ያህል የፀዳ ነው ?

❖**በዛሬው ምንባብ በመወያያ ጥያቄዎቹ ያልተዳሰሰ ሀሳብ ካለ በቀራችሁ ጊዜ ተወያዩበት ።**

### ማጠቃለያ

ሕይወታችንን <u>**ምድራዊ፤ ሥጋዊና አጋንንታዊ ጥበብ**</u> ከተቆጣጠረው የእግዚአብሔርን መንግስት የምናሰፋ ሳንሆን የምናጠብ ο ሌሎችን የምናንጽ ሳንሆን የምናፈርስ ስለምንሆን እነዚህ ባህርያት ውስጣችንን በልተው እንዳይጨርሱት **የ<u>ላይኛይቱ</u>ን የጥበብ** ባሕርያት በራሳችንና በሌሎች ላይ ዕለት ዕለት ትጋት መንፈሳዊ ግንባታ ይጠበቅብናል ።

### በቃል የሚጠና

"ላይኛይቱ ጥበብ ግን በመጀመሪያ ንጽሕት ናት፥ በኋላም ታራቂ፥ ገር፥ እሺ ባይ ምሕረትና በጎ ፍሬ የሞላባት፥ ጥርጥርና ግብዝነት የሌለባት ናት ። "**ያዕ 3:17**

## ጥናት 7
## ለእግዚአብሔር መገዛት
## <u>የምንባብ ክፍል : ያዕ 4:1-12</u>

**መግቢያ:-**ባለፈው ጥናት ምንጫቸው የተለያዩ የሆኑ ከላይ የሚወርድ ፤ የምድር ነው፥ የሥጋም ነው፥ የአጋንንትም ነው ተብለው የተጠቀሱ የጥበብ ዓይነቶችን ምን እንደሚመስሉ በዝርዝር ተመልክተን ነበር ። በዛሬው ጥናታችን ደግሞ ራሳችንን ለእግዚአብሔር ማስገዛት በሚገቡን ተያያዥ እውነቶች ላይ በዝርዝር እንወያያለን ።

**የመወያያ ጥያቄዎች**

1. በቁ.1 ላይ እንደተጠቀሰው በመካከላቸው ለሚፈጠረው **<u>ጦርና ጠብ</u>** መንስዔው ምን እንደሆነ በጥልቀት ተነጋገሩ ።
2. /ከቁ 2-3/ ባለው ክፍል እንደተገለጸው በጥላቻና በብርቱ ራስ-ወዳድነት በመሞላት ከሚደረግ ልመና ምንም መቀበል የማይቻለው ለምን ይመስላችኋል?
3. /ከቁ. 4-5/ ያለውን በመመልከት የዓለም ወዳጅነትን ባሕርያት በመዘርዘር እንዲህ ዓይነቱ ሰው የእግዚአብሔር ጠላት በመሆኑ ምን ሊደርስበት የሚችል ይመስላችኋል?
4. በቁ.6 ላይ እንደምንመለከተው ትዕቢተኞችና ትfከታን ሰዎች ከእግዚአብሔር ዘንድ ምን እንደሚቀበሉ ግለፅ/ጪ።
5. /ከቁ 7-10/ ያለውን በመመልከት ራስን ለእግዚአብሔር ማስገዛት የሚገለጥባቸውን አምስት መንገዶችን በመዘርዘር እያንዳንዱ ምን ማለት እንደሆነ ተወያዩ ።
6. /ከቁ11-12/ እንደተመለከተው እርስ በርስ በመወነጃጀል የእግዚአብሔርን የፍቅር ሕግ እንዴት እንደምንጥስ በማብራራት እውነተኛው ፍርድ ሰጪ ማን እንደሆነ ተነጋገሩ ።

**ከሕይወት ጋር ማዛመድ**

7. በጸሎቶቻችን ጥያቄዎቻችን፤ከትዳር አጋራችን ባለን የየዕለት ግንኙነት ፤ ልጆችን በማሳደግ ሂደት ፤ ከስራ ባልደረቦቻችን ጋር በሚኖረን ውሎ፤ በአገልግሎት ሕብረታችን ምልልስ ወ.ዘ.ተ ራሳችንን ምን ያህል ለእግዚአብሔር እናስገዛለን ?

- **በዛሬው** ምንባብ **በመወያያ ጥያቄዎቹ ያልተዳሰሰ ሀሳብ ካለ በቀራችሁ ጊዜ ተወያዩበት ።**

**ማጠቃለያ**

እንግዲህ ራሳችንን ለእግዚአብሔር ማስገዛት የሚለው ሐሳብ በውስጡ በርካታ ምክሮችን አጭቆ የያዘ እውነት መሆኑን ለመዳሰስ ሞክረናል ። ከነዚህም ጥቂቶቹን ለማስታወስ: ከራስ ወዳድነት ምኞት ያልሆነ ልመና ለእግዚአብሔር ማቅረብ፤ የዓለም ወዳጅ አለመሆን፤ከትዕቢት የጸዳ የትህትና ሕይወት፤ ዲያብሎስን ጸንቶ መቃወም ወይም መቋቋም፤ እጅንም ልብንም ከበደል ማንጻት /ቅድስና ፤ንስሃ ፤ራስን በእዚአብሔር ፊት ማዋረድ፤እርስ በርስ አለመፈራረድ /አለመወነጃጀል ፤ እግዚአብሔር ብቻ ጻድቅፈራጅ እንደሆነ ወዘተ ያጠቃልላል። በእውነቱ ራሳችንን ለእግዚአብሔር እንድናስገዛ ጌታ ጸጋውን ያብዛልን ። አሜን።

**በቃል የሚጠና**

**“** እንግዲህ ለእግዚአብሔር ተገዙ፤ ዲያብሎስን ግን ተቃወሙ ከእናንተም ይሸሻል፤ ወደ እግዚአብሔር ቅረቡ ወደ እናንተም ይቀርባል ። ” **ያዕ 4:7**

**ጥናት 8**
**ስለ ነገ መመካት**
**<u>የምንባብ ክፍል: ያዕ 4: 13 - 17</u>**

**መግቢያ:-**ባለፈው ጥናት ራሳችንን ለእግዚአብሔር ማስገዛት የሚለው ሐሳብ በውስጡ በርካታ ምክሮችን አጭቆ የያዘ እውነት መሆኑን ለመዳሰስ ሞክረናል ። ከነዚህም ጥቂቶቹን ለማስታወስ: ከራስ ወዳድነት ምኞት ያልሆነ ልመና ለእግዚአብሔር ማቅረብ፤ የዓለም ወዳጅ አለመሆን፤ከትዕቢት የጸዳ የትህትና ሕይወት፤ ዲያብሎስን ጸንቶ መቃወም/ መቋቋም፤ እጅንም ልብንም ከበደል ማንጻት /ቅድስና ፤ንስሃ ፤ራስን በእዚአብሔር ፊት ማዋረድ፤እርስ በርስ አለመፈራረድ /አለመወነጃጀል ፤እግዚአብሔር ብቻ ጻድቅ ፈራጅ እንደሆነ ወዘተ እንደሚያጠቃልል በዝርዝር ተመልክተን ነበር ። በዛሬው ጥናታችን ደግሞ ስለ ነገ መመካት እንደማያስፈልግና ስለ ወደፊት ምን ብለን ማቀድ እንደሚገባን የያዕቆብን ምክሮች በአጭሩ እንቃኛለን ።

**የመወያያ ጥያቄዎች**

1. በቁ.13 ላይ ያዕቆብ ስሙ ብሎ ምክሩን መለገስ የሚጀምረው ምን ዓይነት ዕቅድ ላላቸው ሰዎች ነው?
2. በቁ.14 ላይ ያዕቆብ ሕይወትን ከእፋሎት ጋር ያመሳሰለበት ምክንያት ለምንድር ነው?
3. እግዚአብሔር በእቅድ የሚመሩ ሰዎችን ዕቅድና ሥራቸውን የሚቃወመው ይመስላችኋል? ለምን?
4. በቁ.15 ላይ ከተቀመጠው ያያዕቆብ ምክር በመነሳት አማኞች ወደፊት ስለሚያከናውኑት ተግባር ሲያቅዱና ግብ ሲነድፉ ማስቀደም የሚገባቸው ማንን እና ምንን እንደሆነ በጥልቀት ተወያዩ ። /በተጨማሪ ሉቃ 12:16-21 ይመልከቱ/
5. ከቁ 16-17 ባሉት ክፍሎች ውስጥ እንደ ትምክህተኝነትና ኃጢአት እንደመስራት የተቆጠሩት ሐሳቦች ምንድር ናቸው?

**ከሕይወት ጋር ማዛመድ**

6. ከየዕለት ሕይወታችንን ውስጥ በአብዛኛው የምንመራው በእቅድ ነው ወይስ በመላምት ? በዕቅድ የምንመራ ከሆነስ እግዚአብሔርን በማስቀደም ምን ያህል ፈቃዱን እንጠይቃለን?

- ❖ **በዛሬው ምንባብ በመወያያ ጥያቄዎቹ ያልተዳሰሰ ሀሳብ ካለ በቀራችሁ ጊዜ ተወያዩበት ።**

**ማጠቃለያ**

እግዚአብሔር በዕቅድ መመራትን አይቃወምም ። እንዳውም ያበረታታል ። ለምሳሌ በሌሎች ክፍሎች "የእዚአብሔር ቃል ፈረስ ለጦርነት ቀን ይዘጋጃል ድል ግን ከእግዚአብሔር ዘንድ ነው" ። እንዲሁም "የልብ መዘጋጀት ከሰው ነው የምላስ መልስ ግን ከእግዚአብሔር ነው" ይላል ። ነገር ግን አማኞች ወደፊት ስለሚያከናውኑት ተግባር በሚያቅዱበትና ግብ በሚነድፉበት ጊዜ እግዚአብሔርን መጠየቅና ፈቃዱን ማስቀደም ይኖርባቸዋል ። ምክንያቱም እንደ እንፋሎት ቅጽበታዊ በሆነው ምድራዊ ሕይወታችን ለዕቅዶቻችን ስኬት ሰጪው ጌታ ራሱ ነውና ።

**በቃል የሚጠና**

" በዚህ ፈንታ። ጌታ ቢፈቅድ ብንኖርም ይህን ወይም ያን እናደርጋለን ማለት ይገባችኋል ።" **ያዕ 4:15**

## ጥናት 9
## ለጨቋኝ ባለጠጎች ማስጠንቀቂያ
## የምንባብ ክፍል : ያዕ 5÷1-6

**መግቢያ**፦-ባለፈው ጥናት አማኞች ወደፊት ስለሚያከናውኑት ተግባር በሚያቅዱበት ጊዜ እግዚአብሔርን መጠየቅና ፈቃዱን ማስቀደም እንደሚገባቸው ተመልክተን ነበር ። በዛሬው ጥናታችን ደግሞ ፈሪሃ- እግዚአብሔር ለሌላቸው ጨቋኝ ባለ ጠጎች የተሰጠውን ማስጠንቀቂያ በአጭሩ እንቃኛለን ።

**የመወያያ ጥያቄዎች**

1. /ከቁ1-3 /ያዕቆብ ባለ ጠጎችን ዋይ ዋይ እያላችሁ አልቅሱ ብሎ የጠቀሳቸውን ምክንያቶች ዘርዝሩ ።
2. እግዚአብአብሔር ማንቸውንም ባለጠጎ ች በጥቅሉ ወይም ባለጠግነትን በራሱ የሚቃመወም ይመስላችኋል ?
3. /ከቁ. 4-6/ እነዚህ ባለጠጎች በሰራተኞቻቸው የሚፈጽሙትን ጭቆናና በሌሎችም ፃድቃን ሰዎች ላይ የሚያደርሱትን መከራ በመዘርዘር ተወያዩበት ።
4. ስለ ባለ ጠጎችና ገንዘብ መውደድን አስመልክቶ በሌሎች ክፍሎች የተነሱ ሐሳቦችን የሚከተሉትን ጥቅሶች በማንበብ ከአውደ-ምንባቦቹ ሳትወጡ ተወያዩ ። ማቴ 6:24 ፤ ማቴ 19:21-24 ፤ 1 ጢሞ6:6-10
5. ገንዘብ ትክክለኛውን ስፍራ ከያዘ ማለትም እኛ ከመራነው እንደ ታማኝ ሎሌ ሆኖ ያገለግለናል ። በአንፃሩ ደግሞ ገንዘብ እኛን ከተቁጣጠረን እንደ ጨካኝ ጌታ በመሆን ያሰቃየናል ይባላል ። ይህ አገላለጽ ዛሬ ከዳሰስናቸው እውነቶች ጋር ምን ያህል የተቀራረበ ይመስላችኋል ?

**ከሕይወት ጋር ማዛመድ**

6. ገንዘብ ለየዕለት ኑሮአችን መሸፈኛ፤ ለአገልጋዮች ቀለብ፤ ለቤተ ክርስቲያን ግንባታ፤ ለወንጌል ማስፋፊያ ፤ ለልማት ማሳለጫ ወዘተ ጠቃሚ ግብዓት መሆኑን ታምናላችሁ ? ይህ ከሆነ ብልጽግናችንን በአግባቡ ለራሳችንና ለሌሎች ጥቅም እንዲሁም ለእግዚአብሔር ክብር ልንጠቀምበት የምንችለው እንዴት ነው?

- **በዛሬው ምንባብ በመወያያ ጥያቄዎቹ ያልተዳሰሰ ሀሳብ ካለ በቀራችሁ ጊዜ ተወያዩበት ።**

**ማጠቃለያ**

መጽሐፍ ቅዱስ ባለ ጠግነት ኃጢአት ነው፤ ወይም ባለ ጠጎች ሁሉ ፈሪሃ-እግዚአብሔር የላቸውም ብሎ አያስተምርም ። ነገር ግን ያዕቆብ ማስጠንቀቂያ የሚሰጠው ለሃብታቸው በመስገብገብ ሠራተኞቻቸውን ለሚጨቁኑና በሌሎች ንጹሃንም ላይ እስከማስገደል ድረስ ግፍ ለሚፈጽሙ ፈሪሃ-እግዚአብሔር ለሌላቸው ባለ ጠጎች ነው ። ስለዚህ ይህ ማስጠንቀቂያ ባለ ጠጋ ሆነው ለገንዘብ ሳይገዙ ወንጌልን ለማሰራጨትና የተቸገሩትን ለመርዳት ካላቸው ገንዘብ ለጋስ የሆኑ አማኞችን አይመለከትም ። ምክንያቱም ባለ ጠጋ የሆነው ጌታ የሰጣቸውን በረከት በአግባቡ ተጠቅመውበታልና ። በመሆኑም እኛም ከባለ ጠግነት ጋር ተያይዞ የሚመጣውን ክፋትና ዓመጽ በፍፁም በማስወገድ እንደ እግዚአብሔር ሰዎች ከገንዘብ ፍቅር ይልቅ ለጌታ በመገዛት ልንመላለስ ይገባል ።

**በቃል የሚጠና፡**

" እነሆ፥ እርሻችሁን ያጨዱት የሠራተኞች ደመወዝ በእናንተ ተቀምቶ ይጮኻል፥ የአጫጆችም ድምፅ ወደ ጌታ ፀባዖት ጆሮ ገብቶአል ። "**ያዕ 5:4**

## ጥናት 10

## በመከራ መታገስ

**<u>የምንባብ ክፍል ፡ ያዕ 5፥7-12</u>**

**መግቢያ፡**-ባለፈው ጥናት ፈሪሃ-እግዚአብሔር ለሌላቸው ጨቋኝ ባለ ጠጎች የተሰጠውን ማስጠንቀቂያ ተመልክተን ነበር ። በዛሬው ጥናታችን ደግሞ አማኞች ምንም እንኳን በልዩ ልዩ መከራ ውስጥ ቢያልፉም ጸንተው የጌታን ዳግም ምፅዓት በትዕግስት መጠበቅ እንደሚገባቸውና ይህም ዋጋ እንዳለው ያዕቆብ ያበረታታበትን ምክር እናያለን ።

**የመወያያ ጥያቄዎች**

1. /ከቁ.7-8/ እንደተመለከተው ወገኖች ስለሚያልፉበት መከራ ያዕቆብ የመከራቸው እስከ መቼ ድረስ እንዲታገሱ ነው? የመከራው ፍጻሜ ፍሬው መልካም ወይም ክብር መሆኑን ለማበረታታት የሰጣቸውን ምሳሌ አብራሩ ።/ለተጨማሪ ምሳ 27:18ን ይመልከቱ/
2. በቁ.9 ላይ ባለቤቱ በማንኛውም ሰዓት የቤቱን በር ሊከፍት እንድሚችል ሁሉ የጌታ መምጫ ቅርብ መሆኑን አማኞች መገንዘባቸው እርስ በርሳቸው እንዳይወነጃጀሉ እንዴት ሊያግዛቸው ይችላል ?/ለተጨማሪ ማቴ 25፥13ን ይመልከቱ/
3. /ከቁ.10-11/ ባለው ክፍል ቅዱሳን በማንኛውም መከራ ውስጥ ቢያልፉ በእግዚአብሔር ላይ ያላቸውን እምነት ሳይጥሉ ድል መንሳት እንደሚችሉ በትዕግስት ጸንተው ስለ መቆማቸው በምሳሌነት የተጠቀሱትን በመዘርዘር ተወያዩ ።
4. በቁ.12 ላይ እንደተገለጸው አማኞች እርስ በርስ እውነትን መነጋገር እንደሚገባቸውና እውነት ከሆነ **"አዎ"** ካልሆነም **"አይደለም"** ከማለት ባለፈ ተአማኒነትን ለማትረፍ ብለው በማንም በምንም ስም ፈጽሞ መሃላ የተከለከሉት ለምን ይመስላችኋል?

**ከሕይወት ጋር ማዛመድ**

5. እኛስ የክርስቶስ በመሆናችን ምክንያት በሚደርስብን ልዩ ልዩ መከራ በእምነታችን ጸንተን የጌታን ዳግም ምጽዓት ምን ያህል በትዕግስት እየጠበቅነው ነው?

❖ **በዛሬው ምንባብ በመወያያ ጥያቄዎቹ ያልተዳሰሰ ሀሳብ ካለ በቀራችሁ ጊዜ ተወያዩበት ።**

**<u>ማጠቃለያ</u>**

እግዚአብሔር አንዳንዴ በአማኞች ሕይወት ውስጥ እንዲፈጸም የየሚፈቀደው መከራ የመጨረሻ ውጤት ለበጎና መልካም መሆኑን ስንመለከት እኛንም እርሱ ፈቅዶ በምናልፍበት መንገድ በጸጋው አጽንቶ በማቆም ለድል ያበናል ። በመሆኑም በትዕግስትና እግዚአብሔርንም ደስ በሚያሰኝ የፅድቅ ፍሬ የክርስቶስን ዳግም ምፅአት ጸንተን እንድንጠብቅ ጌታ ጸጋውን ያብዛልን ።

**<u>በቃል የሚጠና፡-</u>**

" እናንተ ደግሞ ታገሡ፥ ልባችሁንም አጽኑ፤ የጌታ መምጣት ቀርቦአልና ።" **ያዕ 5:8**

**ጥናት 11**

**የእምነት ፀሎት**

**የምንባብ ክፍል : ያዕ 5÷13-20**

**መግቢያ፡**-ባለፈው ጥናት አማኞች ምንም እንኳን በልዩ ልዩ መከራ ውስጥ ቢያልፉም ጸንተው የጌታን ዳግም ምፅዓት በትዕግስት መጠበቅ እንደሚገባቸውና ይህም ዋጋ እንዳለው ያዕቆብ ያበረታታበትን ምክር ተመልክተን ነበር ። በዛሬው ጥናታችን ደግሞ እንደ እግዚአብሔር ቃል የሚደረግ የጻድቅ ሰው የእምነት ፀሎት በስራዋ እጅግ ኃይልን ማድረግ እንደምትችል የምትችል መሆኑን በዝርዝር እንመለከታለን ።

**የመወያያ ጥያቄዎች**

1. በቁ. 13 "ከእናንተ መከራን የሚቀበል ማንም ቢኖር እርሱ ይጸልይ" ብሎ ያዕቆብ የሚመክረው ለምን ይመስላችኋል?
2. በቁ. 14 አማኝ የሆነ ሰው ሲታመም ምን ማድረግ እንዳለበት ያዕቆብ የሰጣቸውን ምክር በዝርዝር ተወያዩበት ።
3. በቁ. 15 የእምነት ጸሎት ውጤቱ ምን እንደሆነ አብራሩ ።
4. በቁ. 16 ኃጢአትን እርስ በርስ የመናዘዝና አንዱ ስለሌላው የመጸለይ ውጤቱ ምንድር ነው?
5. በቁ. 16 ያዕቆብ "የጻድቅ ሰው ጸሎት በሥራዋ እጅግ ኃይል ታደርጋለች "ይላል ። ለመሆኑ ጻድቅ ሰው ማለት ምን ዓይነት ሰው ይመስላችኋል ?
6. ከቁ. 17-8 እንደተመለከተው እንደ እኛ ሰው የሆነው ኤልያስ በእምነት አጥብቆ በመጸለዩ ምን እንደሆነለት በመዘርዘር ተወያዩ ።
7. ከቁ 19-20 እንደተገለጸው ከእውነት የሳተውን ሰው መመለስ ምን ፋይዳ እንዳለው አብራሩ።

## ከሕይወት ጋር ማዛመድ

8. በክርስቶስ እንደጸደቀ ሰው በእምነት አጥብቃችሁ በመጸለያችሁ በሕይወታችሁ ከተፈጸሙላችሁ የጸሎት መልሶች ጥቂቶቹን ለሕብረታችሁ አጋሩ ።

- **በዛሬው ምንባብ በመወያያ ጥያቄዎቹ ያልተዳሰሰ ሀሳብ ካለ በቀራችሁ ጊዜ ተወያዩበት ።**

## ማጠቃለያ

ዛሬ በተመለከትነው ክፍል በክርስቶስ የጸደቁ አማኞች በእምነት የሚያቀርቡት ጥብቅ ጸሎት በመከራ እንደሚያጸና፤ ሕሙማንን እንደሚፈውስ፤ልዩ ልዩ ተአምራቶችን እንደሚያደርግ ተረድተን እኛም ዘወትር በእምነት ጸሎት በጌታ ፊት ልንተጋ ይገባናል። ጸጋና አቅሙን ያብዛልን ። አሜን !

**በቃል የሚጠና**

" የፃድቅ ሠው ፀሎት በሥራዋ እጅግ ኃይል ታደርጋለች " **ያዕ 5÷16**

# ክፍል ሁለት

## 1ኛው፤ 2ኛው እና 3ውኛ የዮሐንስ

## መልዕክቶች

## 2.1 የሐዋርያው ዮሐንስ መልዕክት - አንደኛ

***መግቢያ፦*** 1ኛ ዮሐንስ መልዕክት ክርስቶስን ማዕከል ያደረገ መልዕክት ነው ። መልዕክቱ የሚጀምረው እንደ ሌሎች የአዲስ ኪዳን መልዕክቶች በሰላምታ ሳይሆን መሰረታዊ በሆነ አስተምህሮ (Fundamental Doctrine) ነው ። ይኸውም በክርስቶስ የተገለጠንን ሕይወት የሚያሳይ፣ ይህ ህይወት ደግሞ ከእግዚአብሔር ጋር እንዲሁም ከልጁ ከኢየሱስ ክርስቶስ ጋር ያለ ህብረት እንደሆነ፣ ህብረቱ ደግሞ ብርሃን በሆነው እግዚአብሔር ፊት በብርሃን መመላለስን እንደሚጠይቅ፣ በአንጻሩ ደግሞ ኀጢአት እንዲሁም ወደ ኀጢአት የሚመራ የተሳሳተ ትምህርት ህብረቱን ሊያጎድፉ እንደሚችል በግልጽ የሚያስተምርና ጥንቃቄ መደረግ እንዳለበትም የሚያሳስብ ነው። በሌላ በኩል ደግሞ ሌሎችን (በዚህ ህብረት ውስጥ የሌሉትን) ወደዚህ ህብረት ይኸውም ከአብ እና ከወልድ ጋር ያለ ህብረት ማለትም የዘላለም ህይወት የሚጋብዝ በዘም ውስጥ ያለው ደስታ ፍጹም እንድሆነ የሚያሳይ መልዕክት ነው። በተጨማሪም መልዕክቱ የሚከተሉትን ሃሳቦች ይዳስሳል ።

- እግዚአብሔርን ማወቅ ትዕዛዙን በመፈጸም እንደሚገለጥ
- ቃሉን በመጠበቅ ውስጥ የእግዚአብሔር ፍቅር ፍጹም እንደሚሆን
- ወንድሙን የሚጠላ በጨለማ ውስጥ እንዳለ
- ዓለምን የሚወድ የአብ ፍቅር በእርሱ ውስጥ እንደሌለ
- ከክርስቶስ ተቃዋሚ መንፈስ ወይም በክርስቶስን የተገለጠውን እውነት የሚቃወም መንፈስ (Antichrist) መጠንቀቅ እንደሚገባ

የፀሐፊው ማንነት በመልዕክቱ ውስጥ አልተጠቀሰም። በመሆኑም መልዕክቱን ከሌሎች የአዲስ ኪዳን መልዕክቶች/ደብዳቤዎች ትንሽ ለየት እንዲል አድርጎታል። በአዲስ ኪዳን ውስጥ ካሉ መልዕቶች መካከል ከዕብራውያን መልዕክት በተጨማሪ የፀሐፊው ማንነት ያልተጠቀሰበት መልዕክት ይሄ የ1ኛ ዮሐንስ መልዕክት ነው ። ምንም እንኳን ፀሐፊው በመልዕክቱ ውስጥ እራሱን በስም ለይቶ ባይጠቅስም ከዚህ በታች የተዘረዘሩት እውነታዎች ሐዋሪያው ዮሐንስ መሆኑን በደንብ ያመለክታሉ ።

1. የፅfhፉ ይዘት፣ የአፃፃፍ ዘይቤውና የቃላት ምርጫው ሐዋሪያው ዮሐንስ ከጻፈው የዮሐንስ ወንጌል ጋር በጣም ይመሳሰላል። በንጽጽር የተቀመጡ ለምሳሌ ብርሃንና ጨለማ፣ሕይወትና ሞት፣እውነትና ሐሰትእንዲሁም ፍቅርና ጥላቻ ወዘተ የመሳሰሉ የሚቃረኑ ወዘተ የመሳሰሉት ሐሳቦች ሐዋርያው ዮሐንስ በጻፈው በዮሐንስ ወንጌል ላይም በተመሳሳይ ሁኔታ ተጠቅሰዋል ።
2. ፀሐፊው በቅርብ የነበረ የኢየሱስ ክርስቶስ የዓይን ምስክር እንደሆነ በክፍሉ መጀመሪያ ላይ በእርግጠኛነት ጠቅሷል። (1ኛ ዮሐ 1:1-4) በዮሐንስ ወንጌል 21:20-24 ላይ ዮሐንስ ከጌታ ኢየሱስ ጋር ቅርበት እንደነበረው በተመሳሳይ ሁኔታ እና በግልጽ ተቀምጧል።
3. ዮሐንስ እራሱን በወል ስም የመጥራት ተለምዶ ነበረው። ከዚህ ቀጣይ በሆኑት በ2ኛ እና በ3ኛ መልዕክቶች መግቢያ ላይ ዮሐንስ እራሱን ሽማግሌው በማለት ሲጠቅስ በተመሳሳይ ሁኔታ በዮሐንስ ወንጌል ላይ ደግሞ ኢየሱስ ይወደው የነበረው በማለት ማንነቱን ስሙን ሳይጠቅስ ነገር ግን በሌላ መልኩ ሲገልጽ ይታያል።
4. በተጨማሪም ፕሊካርፕን (Bishop Polycarp) ጨምሮ የቤተክርስቲያን አባቶች ፀሐፊው ሐዋሪያው ዮሐንስ እንደሆነ ይመሰክራሉ። ፖሊካርፕ በሁለተኛው ምዕተ-ዓመት መጀመሪያ ላይ የነበረ ቄስ እና ሐዋሪያው ዮሐንስን በግል የሚያውቀው እንደ ነበር እንዲሁም የሰምሬኔስን ቤተክርስቲያን በመሪነት ያገለገለ እንደነበር ይነገራል። ምንጭ: https://zondervanacademic.com/blog/who-wrote-1-2-3-john

### የመልዕክቱ ተደራሲያን

የመልዕክቱ ቀጥታ ተቀባይ ሆኖ በስም የተጠቀስ ቤተክርስቲያንም ይሁን ግለሰብ አለመኖሩ መልዕክቱ በሁሉም ዘመን ለሚኖሩ ክርስቲያኖች የተፃፈና አጠቃላይ ይዘት (General Epistle) ያለው እንዲሆን አድርጎታል ። ጸሃፊው የመልዕክቱ አንባቢዎች በተለያየ መንፈሳዊ ህይወት ደረጃ ላይ ላሉ በሁሉም ዘመን የሚኖሩ ክርስቲያኖችን የሚመለከት ይዘት ሰጥቶታል ። 1ኛ የዮሐንስ 2:12-14 ላይ እነዚህንም አማኞች በሦስት ደረጃ ከፍሎ ያሳያል ።

- **ልጆች ሆይ**: ኃጢአታችሁ ስለ ስሙ ተሰርዮላችኋልና፣ አብን ዐውቃችሁታልና - እነዚህ አዲስ አማኞች ወይም በቅርብ ጊዜ ዳግም ውልደት ያገኙ
- **ጎበዞች ሆይ**: ክፉውን አሸንፋችኋልና፣ ብርቱዎች ስለሆናችሁ፣ የእግዚአብሔርም ቃል በእናንተ ስለሚኖር - እነዚህ በእግዚአብሔር ቃል የበሰሉትን ሲሆን
- አባቶች ከመጀመሪያ ያለውን እርሱን አውቃችሁታልና - እነዚህ በእግዚአብሔር ቤት ውስጥ የቆዩና በክርስትና ሕይወታቸው የበሰሉ ሊሆኑ ይችላሉ ።

ይሁን እንጂ ዮሐንስ ይህንን ደብዳቤ በወቅቱ በአስቸጋሪ ሁኔታና ተግዳሮት ውስጥ እያለፉ ያሉ በትንሿ እስያ (Asia Minor) በአሁኑ ጊዜ ደግሞ ቱርክ (Turkey) ተብሎ በሚጠራው አገር ይኖሩ የነበሩ ክርስቲያኖችንም የሚመለከት እንደሆነ 1 ዮሐ 2:20 እና 1 ዮሐ 2:27 ላይ ያሉ ሃሳቦች ይጠቁማሉ። እንደ መልዕክቱ አገላለጽ የተግዳሮቱም ዋና መንስኤ ከመካከል ተገንጥለው የወጡ የክርስቶስን መሢህነትና የእግዚአብሔር ልጅነት የካዱ ሰዎች በአካባቢው ያሉትን በእምነታቸው የጸኑት ክርስቲያኖችን ማጥቃት መጀመራቸው ነበር ።

### መልዕክቱ የተጻፈበት ዘመን

መልዕክቱ የተጻፈበትን ጊዜ በትክክል ማስቀመጥ ትንሽ አስቸጋሪ ነው ። ነገር ግን **(1)** የሌሎች ክርስቲያን ጸሐፊዎች ምስክርነት፣ **(2)** የኖስቲዝም (gnosticism) ስህተት ትምህርት በመልዕክቱ ላይ መወገዙ፣ **(3)** ዮሐንስ በእድሜው የገፋ መሆኑን የሚያመለክቱ አገላለጾች መኖራቸው መልዕክቱ በመጀመሪያው ምእተ ዓመት መጀመሪያ አካባቢ እንደተጻፈ ይጠቁማሉ ። ስለዚህም የ1ኛ ዮሐንስ መልዕክት የተፃፈው ምናልባትም በ85-95 A.D. መካከል ባለው ጊዜ ውስጥ ሳይሆን አይቀርም ተብሎ ይገመታል ።

### ታሪካዊ ዳራ

ምንም እንኳ ዮሐንስ ይህንን ደብዳቤ ሲጽፍ እድሜው የገፋ ቢሆንም በስፍራው በነበሩ አብያተ ክርስቲያናት በንቃት እያገለገለ እንደነበር ይነገራል። ዮሐንስ በወቅቱ በሕይወት የነበረ ብቸኛው ሐዋርያ እና የክርስቶስን ምድራዊ አገልግሎት፣ ሞቱን፣ ትንሳኤውንና እርገቱን በቅርብ በዐይን ያየ ከኢየሱስ ጋር የጠበቀ ግንኙነት የነበረው ሕያው የዓይን ምስክር ነበረ። መልእክቱ በተጻፈበት ጊዜ የነበሩ አማኞች በወቅቱ ከነበርው የኖስቲዝም (Gnosticism) የስህተት ትምህርት ጋር ፊት ለፊት የተፋጠጡበት ጊዜ ነበር። ከኖስቲዝም (Gnosticism) የስህተት ትምህርት እና መናፍቃዊ አመለካከቶች የተነሳ ከልክ ያለፈ ነጻነትና ልቅነት ዘመኑን አጥለቅልቆ የሥነ ምግባር ሕጎች የተጣሱበት ጊዜ ነበር። ከኖስቲዝም (gnosticism) አደገኛ የስህተት ትምህርት የተወለደ መናፍቃዊ አመለካከት አንዱ፦ አንድ ሰው በአካሉ የሚፈጽመው ኃጢአት ከመንፈሱ ጋር ግንኙነት እንደሌለውና መንፈሳዊ ህይወቱ ላይ ምንም ዓይነት አሉታዊ እንድምታ (Negative Implication) አያመጣም የሚል ነበር። ይህ አስተምሮ በጣም አደገኛ የሆነ መናፍቃዊ አስተምሮ ሲሆን መሰረት የሚያደርገውም እውነት ላይ ሳይሆን ስሜታዊና የማይጨበጥ ፈጽሞ ከእውነታው የራቀ ሃይማኖታዊ ቅዠት ላይ ነው።

**የመልዕክቱ ዓላማ**

ዮሐንስ ልክ በወንጌሉ ላይ እንዳደረገው በዚህም የ1ኛ ዮሐንስ መልዕክት ላይ አላማውን ግልፅ በሆነ መንገድ አስቀምጧል፡፡ ለዚህ ደብዳቤ ተቀባይ/አንባቢ ለሆኑ አማኞች ከእግዚአብሔር አብ እና ከልጁም ከኢየሱስ ክርስቶስ ጋር ያለ እውነተኛ የሆነ ሕብረት መሰረቱ ምን እንደሆነና ይህም ሕብረት የሚያመጣውን ደስታ እንዲረዱ፣ ሕብረቱን ሊያጎድፉ ከሚችሉ ነገሮች ደግሞ መጠንቀቅ እንዳለባቸው ለማሳሰብ ነው ።

**1. ስለ እምነታቸው እንዲያውቁና እርግጠኛ እንዲሆኑ**

- ከአብና ከወልድ ጋር ባለ የጠለቀ ሕብረት ውስጥ ደስታቸው ፍጹም እንደሚሆን " ደስታችሁም እንዲፈጸም ይህን እንጽፍላችኋለን ። " 1ኛ ዮሐ 1:4
- ሰለ ተሰጣቸው የዘላለም ሕይወት እርግጠኞች እንዲሆኑ "በእግዚአብሔር ልጅ ስም የምታምኑ እናንተ፣ የዘላለም ሕይወት እንዳላችሁ ትውቁ ዘንድ ይህን እጽፍላችኋለሁ ። 1ኛ ዮሐ 5:13

**2. በእምነታቸው ጸንተው እንዲቆሙ**

- "እናንተ ግን ከእርሱ ከቅዱሱ፣ ቀባት አላችሁና፤ ሁላችሁም እውነትን ታውቃላችሁ"1ኛ ዮሐ 2:20
- እናንተስ **<u>ከመጀመሪያ የሰማችሁት</u>** <u>በእናንተ</u> **<u>ጸንቶ</u>** ይኑር። ከመጀመሪያ የሰማችሁት በእናንተ ቢኖር፥ እናንተ ደግሞ በወልድና በአብ ትኖራላችሁ ።" 1ኛ ዮሐ 2:24
- "ልጆች ሆይ፤ ማንም እንዳያስታችሁ ተጠንቀቁ፤ እርሱ ጻድቅ እንደሆነ፣ ጽድቅን የሚያደርግ ጻድቅ ነው።" 1ኛ ዮሐ 3:7

**3. እምነታቸው እንዳይበረዝ እንዲጠነቀቁ**

- **ከሐሰተኛ አማኞች**

"ከእኛ ዘንድ ወጡ፥ ዳሩ ግን ከእኛ ወገን አልነበሩም፤ ከእኛ ወገንስ ቢሆኑ ከእኛ ጋር ጸንተው በኖሩ ነበር፤ ነገር ግን ሁሉ ከእኛ ወገን እንዳልሆኑ ይገለጡ ዘንድ ወጡ። "1ኛ ዮሐ 2:19

- **ከሐሰተኛ** አስተ**ማሪዎች**

" ስለሚያስቱአችሁ ሰዎች ይህን ጽፌላችኋለሁ። እናንተስ ከእርሱ የተቀበላችሁት ቀባት በእናንተ ይኖራል፥ ማንም **<u>ሊያስተምራችሁ አያስፈልጋችሁም፤</u>** ነገር ግን የእርሱ ቀባት ስለ ሁሉ እንደሚያስተምራችሁ፥ እውነተኛም እንደ ሆነ ውሸትም እንዳልሆነ፥ እናንተንም እንዳስተማራችሁ፥ በእርሱ ኑሩ ። "1ኛ ዮሐ 2:26-27

- **ከሐሰተኛ ነብያት**

"ወዳጆች ሆይ፤ <u>መንፈስን ሁሉ አትመኑ</u>፤ ነገር ግን <u>መናፍስት ከእግዚአብሔር መሆናቸውን መርምሩ</u>፤ ምክንያቱም ብዙ ወደ ዓለም ወጥተዋልና። እግዚአብሔርን መንፈስ በዚህ ታውቃላችሁ፤ ኢየሱስ ክርስቶስ በሥጋ እንደ መጣ የሚታመን መንፈስ ሁሉ ከእግዚአብሔር ነው፥ ኢየሱስ ክርስቶስም በሥጋ እንደ መጣ የማይታመን መንፈስ ሁሉ ከእግዚአብሔር አይደለም፤ ይህም የክርስቶስ ተቃዋሚው መንፈስ ነው፤ ይህም እንዲመጣ ሰምታችኋል፥ አሁንም እንኳ በዓለም አለ። "1ኛ ዮሐ 4:1-3

- **ከዓለም**

"ልጆች ሆይ፥ እናንተ ከእግዚአብሔር ናችሁ አሸንፋችኋቸውማል፥ በዓለም ካለው ይልቅ በእናንተ ያለው ታላቅ ነውና። እነርሱ **<u>ከዓለም</u>** ናቸው፤ ስለዚህ ከዓለም የሆነውን ይናገራሉ <u>ዓ**ለሙም**</u> ይሰማቸዋል።
6 እኛ ከእግዚአብሔር ነን፤ እግዚአብሔርን የሚያውቅ ይሰማናል፤ ከእግዚአብሔር ያልሆነ አይሰማንም። የእውነትን መንፈስና የስሕተትን መንፈስ በዚህ እናውቃለን። "1ኛ ዮሐ 4:4-6

## ጥናት 1
## በብርሃን መመላለስ
## <u>የምንባብ ክፍል: 1ኛ ዮሐ 1፡1-10</u>

**መግቢያ** ፦ በዛሬው የመጀመሪያ ጥናታችን አማኞች ከአብ እና ከወልድ ጋር ያለው ሕብረት ምን እንደሚመስልና ይህ እውነተኛ ሕብረት በብርሃን ስንመላለስ እንደሚገለጥና ሕብረቱን ደግሞ ምን ሊያበላሸው እደሚችል በዝርዝር እንመለከታለን ።

**<u>የመወያያ ጥያቄዎች</u>**

1. ከቁ. 1-2 ባለው ክፍል ዮሐንስ "ከመጀመሪያው የነበረውንና የሰማነውን በዓይኖቻችንም ያየነውን የተመለከትነውንም እጆቻችንም የዳሰሱትን" ብሎ የሚገልፀው ስለ ምን እንደሆነ ተወያዩ ።
2. በ ቁ. 3 ላይ የተጠቀሰው ህብረት ምንን መሰረት ያደረገ ህብረት እንደሆነ ተወያዩ ።
3. እግዚአብሔር ብርሃን ነው ሲል ምን ማለት እንደሆነ ቁ. 5ን እንደመነሻ ሃሳብ በመጠቀም ተወያዩ ።
4. ዮሐንስ ጨለማን የሚያዛምደው ከምን ጋር ነው? ቁ.6-10 መሰረት በማድረግ ተወያዩ ።
5. ከእግዚአብሔር ጋር ያለንን እውነተኛ ህብረት ሊያጎድፍ/ሊያበላሽ የሚችለው ዋና ችግር ምንድነው? በምንስ ይቀረፋል ቁ.6-10

**<u>ከዕለታዊ ኑሮና መንፈሳዊ ሕይወታችን ጋር ማዛመድ</u>**

6. በብርሃን ለመመላለስ ምን ዓይነት ተግባራዊ የክርስትና ሕይወት እንደሚጠበቅብን ተሞክሮአችሁን አጋሩ ።

- **በዛሬው ምንባብ በመወያያ ጥያቄዎቹ ያልተዳሰሰ ሀሳብ ካለ በቀራችሁ ጊዜ ተወያዩበት ።**

**<u>ማጠቃለያ</u>**

ለመዳሰስ እንደሞከርነው ትክክለኛና እውነተኛ ሕብረት አለን ማለት የምንችለው ብርሃን ከሆነው ከእግዚአብሔር ጋር ስለሆነ በፊቱ በብርሃን ልንመላለስ ይገባናል ። በዚህም ህብረት ውስጥ እግዚአብሔር ታላቅ የሆነ ደስታ ያጎናጽፈናል ።

**<u>በቃል የሚጠና</u>**

" ከእርሱም የሰማናት ለእናንተም የምናወራላችሁ መልእክት። እግዚአብሔር ብርሃን ነው ጨለማም በእርሱ ዘንድ ከቶ የለም የምትል ይህች ናት።" 1ኛ ዮሐ 1:5

## ጥናት 2
## የመታዘዝ ሕይወት
### <u>የምንባብ ክፍል ፦ 1ኛ ዮሐ 2 ፥ 1-17</u>

**መግቢያ** ፦ ባለፈው ጥናት አማኞች ከአብ እና ከወልድ ጋር ያለው ሕብረት ምን እንደሚመስልና ይህ እውነተኛ ሕብረት በብርሃን ስንመላለስ እንደሚገለጥና ሕብረቱን ደግሞ ምን ሊያበላሸው እደሚችል ተመልክተን ነበር ። በዛሬው ጥናታችን ደግሞ እግዚአብሔርን ማወቃችን ወገኖችን በመውደድ፣ዓለምን ባለመውደድ ና ከኃጢአት በመራቅ ሊታይ እንደሚገባው ሐዋርያው ዮሐንስ በተለያ የብስለት ደረጃ ለሚገኙ ቅዱሳን በአጽንዖት ያቀረበላቸውን ምክር በዝርዝር እንቃኛለን ።

**የመወያያ ጥያቄዎች:**

**1.** ዮሐንስ አንባቢዎቹን ልጆቼ ሆይ ብሎ ለምን እንደጠራና መልዕክቱን የፃፈበትን ምክንያተ-ሃሳቦች ተወያዩ።

**2.** በቁ. 3-6 መሰረት እግዚአብሔርን ማወቃችን የሚገለጠበት ዋና መንገድ ምንድነው?

**3.** በብርሃን መመላለስ የሚገለጸው እንዴት ነው? ቁ. 7-11

**4.** ከ ቁ. 12-14 ባለው ክፍል ሐዋርያው ዮሐንስ ልጆች ሆይ፣ባቶች ሆይ ጎበዞች ሆይ በማለት የተጠቀመባቸውን አገላለፆችና የሰጣቸውን ምክሮች ተወያዩ።

**5.** ከቁ. 15-17 "ዓለምን ወይም በዓለም ያለውን ማናቸውንም ነገር አትውደዱ።" በሚለው ሃሳብ ውስጥ በዓለም ያለው ምን እንደሆነና አትውደዱ የተባለበትስ ምክንያት ምን እንደሆነ ተወያዩ ።

### ከሕይወት ጋር ማዛመድ

**6.** ለእግዚአብሔር ክብር የመስዋዕትነትና የመታዘዝ ህይወት እንዳንኖር ለምን እንደሚያዳግተን ከግል ተሞክሮአችሁ በመነሳት ለህብረቱ አካፍሉ ።

- ❖ **በዛሬው ምንባብ በመወያያ ጥያቄዎቹ ያልተዳሰሰ ሀሳብ ካለ በቀራችሁ ጊዜ ተወያዩበት ።**

### ማጠቃለያ

መፅሐፍ ቅዱሳዊ የሆነ መታዘዝ፣ እውነተኛ ፍቅርና ዓለምን አለመውደድ ምን እደሚመስሉ ተመልክተናል። ዮሐንስ በክፍሉ ላይ እንደገለጸው ይህ አዲስ ትዕዛዝ ሳይሆን የነበረ ትዕዛዝ ስለሆነ በዚህ ዘመን የምንገኘኝ እኛም ዛሬ ለሰማነው የእግዚአብሔር ቃል እንድንታዘዝ ጌታ ጸጋውን ያብዛልን ።

### በቃል የሚጠና

" ትእዛዛቱንም ብንጠብቅ በዚህ እንዳወቅነው እናውቃለን ። " 1ኛ ዮሐ 2:3

## ጥናት 3
## ክክርስቶስ ተቃዋሚዎች መጠንቀቅ
**<u>የምንባብ ክፍል፦ 1ኛ ዮሐ2፥18 -27</u>**

**መግቢያ** ባለፈው ጥናት እግዚአብሔርን ማወቃችን ወገኖችን በመውደድ፣ዓለምን ባለመውደድ ና ከኃጢአት በመራቅ ሊታይ እንደሚገባው ሐዋርያው ዮሐንስ በተለያ የብስለት ደረጃ ለሚገኙ ቅዱሳን በአጽንዖት ያቀረበላቸውን ምክር በዝርዝር ተመልክተን ነበር። በዛሬው ጥናታችን ደግሞ በዘመኑ ስለነበሩየክርስቶስ ተቃዋሚዎች እንዲሁም በመጨረሻ ሰዓት ከሚገለጠው የክርስቶስ ተቃዋሚ እንዴት መጠንቀቅ እንዳለብን እንመለከታልን ።

**የመወያያ ጥያቄዎች:**

1. በቁ. 2:18 መሰረት የመጨረሻው ሰዓት እንደሆነ መገለጫው ምንድነው?
2. ይመጣል በተባለው የክርስቶስ ተቃዋሚ እና ብዙ የክርስቶስ ተቃዋሚዎች መጥተዋል በተባሉት መካከል ያለውን ልዩነትና ተመሳሳይነት ተወያዩ ።
3. ቁ. 19 ላይ "ከእኛ መካከል ወጡ፤ ይሁን እንጂ ከእኛ ወገን አልነበሩም" የተባሉት እነማን እንደሆኑ የክፍሉን አጠቃላይ አውድ በመመልከት ተወያዩ።
4. ቁ. 24 "ከመጀመሪያ የሰማችሁት" የሚለውን ቁ. 25 ላይ ከተሰጠው ሃሳብ ጋር በማያያዝ በዝርዝር ተወያዩ።
5. ቁ. 27 "የተቀበላችሁት ቅባት ስለ ሁሉም ነገር ያስተምራችኋል" የሚለው ሃሳብ ምን ማለት እንደሆነ የሰውን ልምምድ ሳይሆን የእግዚአብሔርን ቃል መሰረት ባደረገ መልኩ ተወያዩ ።

**ከሕይወት ጋር ማዛመድ**

6. አሁን ባለንበት ዘመን እውነትን በሚበርዝና ክርስቶስን በሚሸፍን ብዙ እንቅስቃሴዎችን ቤተክርቲያን እየተጋፈጠች ያለችበት ጊዜ በመሆኑ ከእግዚአብሔር ቃል የተረዳነው እውነት እንዳይበረዝ ምን ማደርግ አልብን ትላላችሁ?

- **በዛሬው ምንባብ በመወያያ ጥያቄዎቹ ያልተዳሰሰ ሀሳብ ካለ በቀራችሁ ጊዜ ተወያዩበት ።**

**ማጠቃለያ**

በዛሬው ጥናታችን ከክርስቶስ ተቃዋሚዎች እንዴት መጠንቀቅ እንዳለብን ተመልክተናል። የክርስቶስ ተቃዋሚዎች የሚያስቱበት ዋናው መንገድ የክርስቶስን አዳኝነት በመሸፈን ስለሆነ መከላከያ መንገድ አድርገን ልንጠቀም የሚገባን የእግዚአብሔር ቃል ስለ ክርስቶስ የተጻፈውን ከመጀመሪያ የሰማነውን፣ የማይቀየረውን እውነት አጥብቀን በመያዝ ነው።

**በቃል የሚጠና**

" እናንተስ ከመጀመሪያ የሰማችሁት በእናንተ ጸንቶ ይኑር። ከመጀመሪያ የሰማችሁት በእናንተ ቢኖር፥ እናንተ ደግሞ በወልድና በአብ ትኖራላችሁ። "1ኛ ዮሐ 2:2

## ጥናት 4

## የአማኞች ፍቅር

## <u>የምንባብ ክፍል : 1ኛ ዮሐ 3:1-24</u>

**መግቢያ**፡ ባለፈው ጥናት ይህ ዘመን የመጨረሻው ዘመን እንደሆነና እንዴት ከክርስቶስ ተቃዋሚዎች መጠንቀቅ እንዳለብን ተመልክተን ነበር ። በዛሬው ጥናታችን ደግሞ የእግዚአብሔር ልጆች በእግዚአብሔር ፊት ሊኖረን ስለሚገባ ድፍረት በእግዚአብሔር መታመን እንደሚገባንና ፤ እንዲሁም እርስ በርሳችን መዋደድ እንዳለብን እናያለን ።

**የመወያያ ጥያቄዎች**

1. በቁ 3 “በእርሱም ይህን ተስፋ የሚያደርግ ሁሉ እርሱ ንጹሕ እንደ ሆነ ራሱን ያነጻል።” የሚለው ምንባብ ከእግዚአብሔር እና ከስው ባህሪያት ጋር በማነጻጸርር ተወያዩበት።
2. የእግዚአብሔር ልጆች እና የዲያቢሎስ ልጆች ባህሪያት ልዩነት በደንብ አብራሩ።
3. ከቁ.10-15 ስለ መውደድ እና ስለ መጥላት የተነገሩትን መመሪያዎች በማንበብ በእነዚህ ሁለት ሃሳቦች ላይ ተመስርታችሁ በጥልቅ ተወያዩባቸው።
4. የእግዚአብሔር ፍቅር በእኛ ውስጥ እንዳለ የምናሳይባቸው ተግባራት ከቁ 16-18 ያለትን ሃሳቦች በመዘርዘር ተወያዩባቸው።
5. በቁ 23-24 ላይ የተጠቀሱት የእግዚአብሔር ትእዛዛት በመዘርዘር አብራሩ ።
6. በቁ 22 “...የምንለምነውን ሁሉ ከእርሱ እናገኛለን ።” የምንለምነውን የማናገኘው እግዚአብሔር ስለማይሰማ ነው ወይስ እኛ የምንለምነውን ስለማናውቅ ነው? መልሳችሁ በእግዚአብሔር ቃል የተመሰረተ ይሁን።

**ከሕይወት ጋር ማዛመድ**

7. በሕይወታችሁ እግዚአብሔር አይከብርበትም የምትሏቸውና፤ እግዚአብሔር ከሕይወታችሁ እንዲያስውግዳቸው የምትፈልጎቸውን ልምምዶች ካሉ አብራቹህ ተወያዩባቸው ።

- **በዛሬው ምንባብ በመወያያ ጥያቄዎቹ ያልተዳሰሰ ሀሳብ ካለ በቀራችሁ ጊዜ ተወያዩበት ።**

**ማጠቃለያ**

እግዚአብሔር በፍፁም ፍቅሩ ወዶን ልጆቹ እንድንሆን ከመርጠን እኛም በእግዚአብሔር እንደተወደዱ ልጆች እርስ በርስ በመዋደድ በሁለንተናችን የእግዚአብሔርን ፍቅር ልናሳይ ይገባናል።

**በቃል የሚጠና**

“ልጆቼ ሆይ፥ በሥራና በእውነት እንጂ በቃልና በአንደበት አንዋደድ” 1ኛ ዮሐ 3፤18

# ጥናት 5
# መንፈስን መርምሩ
## <u>የምንባብ ክፍል: 1ኛ ዮሐ 4:1-21</u>

**መግቢያ፡** ባለፈው ጥናት የእግዚአብሔር ልጆች በእግዚአብሔር ፊት ሊኖረን ስለሚገባ ድፍረት በእግዚአብሔር መታመን እንደሚገባንና ፤ እንዲሁም እርስ በርሳችን መዋደድ እንዳለብን ተመልክተን ነበር ። በዛሬው ጥናታችን ደግሞ መንፈስን መመርመር እንደምንችል፤ እግዚአብሔር እንዴት አድርጎ እንደወደደን እና እርስ በርሳችንም መዋደድ እንዳለብን እናያለን ።

**የመወያያ ጥያቄዎች**

1. መናፍስት ከእግዚአብሔር እንደሆኑ እንዴት አድርገን ልንመረምር እንችላለን?
2. አማኞች የእግዚአብሔርን ሃሳብና ፈቃድ በዚህ ዘመን ለማወቅ ማወቅ ያለባቸው ነገሮች ምን ምን ናቸው?
3. እግዚአብሔር የወደደን እንዴት አድርጎ ነው? እርሱ እንዲህ ከወደደን እኛስ እርስ በርሳችን መዋደድ ያለብን እንዴት ነው?
4. በፍፁም ፍቅር እና በፍርሃት መካከል ያለውን ልዩነት ምን እንደሆነ አብራሩ ።
5. እግዚአብሔርን የሚወድ ሰው ሊታይበት የሚገቡ ባሕርይ ምን እንደሆነ ነው ቃሉ የሚያዘው?

**ከሕይወት ጋር ማዛመድ**

6. ከእግዚአብሔር ቃል ውጭ የሆነ ልምምድ በግልም ሆነ በህብረት ውስጥ ሲያጋጥም በፍቅርእንዴት ማስተካከል እንደሚቻል አብራራ/ሪ።

- ❖ **በዛሬው ምንባብ በመወያያ ጥያቄዎቹ ያልተዳሰሰ ሀሳብ ካለ በቀራችሁ ጊዜ ተወያዩበት ።**

**ማጠቃለያ**

በዚህ ባለንበት ዘመን ውስጥ ብዙ ከእግዚአብሔር ያልሆኑ የተሳሱቱ ትምህርቶች የበዙበት ዘመን ነው፤ ክርስቲያኖች ከመቸውም ይልቅ ክፉውን ከመልካሙ፤ እውነቱን ከውሸቱ መለየት በሚያስችለን በእግዚአብሔር ቃል እና በመንፈስ ልንመላለስ ያስፈልገናል ።

**በቃል የሚጠና**

“ወዳጆች ሆይ፥ መንፈስን ሁሉ አትመኑ፥ ነገር ግን መናፍስት ከእግዚአብሔር ሆነው እንደ ሆነ መርምሩ፤ ብዙዎች ሐሰተኞች ነቢያት ወደ ዓለም ወጥተዋልና። ” **1ኛ ዮሐ 4:1**

## ጥናት 6
## በክርስቶስ ማመን
## የምንባብ ክፍል :1ኛ ዮሐ 5:1-12

**መግቢያ፡** ባለፈው ጥናት መንፈስን መመርመር እንደምንችል፤ እግዚአብሔር እንዴት አድርጎ እንደወደደን እና እርስ በርሳችንም መዋደድ እንዳለብን ተመልክተን ነበር ። በዛሬው ጥናታችን ደግሞ በእግዚአብሔር ልጅ ላይ ስላለን እምነትና በዚህ እምነት እንዴት አለምን ማሸነፍ እንድምንችል እንቃኛለን ።

**የመወያያ ጥያቄዎች**

1. ከእግዚአብሔር የመወለዳችን ዋነኛ መገለጫ ምንድር ነው?
2. "…በእግዚአብሔር ልጅ የሚያምንበነፍሱ ምስክር አለው" የሚለውን ቃል ተወያዩብት።
3. አንድ አማኝ በእግዚአብሔር ፊት ድፍረት ሊኖረው የሚችለው እንዴት ነው?
4. ወደ እግዚአብሔር በልመና ስንቀርብ ልመናችን እንዴት መሆን አለበት?
5. ይህንን አለም ማሸንፍ የምንችለው እንዴት አድርገን ነው?

**ከህይወት ጋር ማዛመድ**

6. በመንፈሳዊ ሕይወታችን እንዳናድግ እንቅፋት እየሆኑብን ያሉ ነገሮች ምን ምን ናቸው ብላችሁ ታምናላችሁ?

- ❖ **በዛሬው ምንባብ በመወያያ ጥያቄዎቹ ያልተዳሰሰ ሀሳብ ካለ በቀራችሁ ጊዜ ተወያዩበት ።**

**ማጠቃለያ**

በእግዚአብሔር ልጅ ለምናምን ለሁላችን የዘላለም ሕይወት እንዳለን ማወቃችን ለክርስትና ህይውታችን እጅግ አስፈላጊ ነው ። ይህን የዘለዓለም የሕይወት ዋስትና ክርስቶስን በማመን ማግኘታችንና መያዛችን የአሁኑን ዓለም የምናሸንፍበት መንፈሳዊ አቅም ይሆነናል ። በምድር ስንመላለስ ደግሞ እኛ በተወደድንበት ፍቅር ሌሎችን በመውደድ ትዕዛዙን እንድንፈጽም ያግዘናል። ይህን ያደረገ ጌታ ስሙ ለዘለዓለም የተባረከ ይሁን።

**በቃል የሚጠና**

"ክርስቶስ ነው ብሎ በኢየሱስ የሚያምን ሁሉ ከእግዚአብሔር ተወልዶአል፥ ወላጁንም የሚወድ ሁሉ ከእርሱ የተወለደውን ደግሞ ይወዳል። " 1ዮሐ5:1

## ጥናት 7

## የማጠቃለያ ምክር

**<u>የምንባብ ክፍል፡ 1ኛ ዮሐ 5፤13-21</u>**

**መግቢያ፡** ባለፈው ጥናት ክርስቶስ ነው ብሎ በኢየሱስ የሚያምን ሁሉ ከእግዚአብሔር መወለዱንና ከእግዚአብሔር የተወለደ ሁሉ ዓለምን እንደሚያሸንፍ ተመልክተን ነበር። በዛሬው ጥናታችን ደግሞ በእግዚአብሔር ልጅ በማመናችን ምክንያት የዘላለም ህይወት እንዳለን እናያለን።

### የመወያያ ጥያቄዎች

1. በቁ 13 ሐዋርያው ዮሐንስ ይህንን መልዕክት ምን እንዲያውቁ እንደጻፈላቸው ተወያዩ ።
2. (ቁ 14-15) ሐዋርያው ዮሐንስ በእግዚአብሔር ዘንድ ያለን ድፍረት ምንድን ነው ይለናል? ጸሎትን አስመልክቶ የተሰጠው መመሪያዎችስ ምን ምን ናቸው?
3. “ሞት የማይገባውን ኃጢአት እና የሚገባው ኃጢአት” ከሚለው ሐሳብ ምን ትረዳላችሁ ?
4. በቁ 18፣19 ላይ ‹‹እናውቃለን›› የሚለው አነጋገር ያጠቃለላቸው ሃሳቦች ምንድር ናቸው?
5. በቁ 20፣21 የእግዚአብሔርም ልጅ በመምጣቱ ምን ሆነ ይለናል? “እርሱ እውነተኛ አምላክና የዘላለም ሕይወት ነው” የተባለው ማን ነው?

### ከሕይወት ጋር ማዛመድ

6. በዚህ እኛ በምንኖርበት ዘመን በራሳቸው ክፉ ያልሆኑ ነገር ግን ካልተጠነቀቅን በሕይወታችን እንደ ጣዖታት ሊሆኑብን የሚችሉ ነገሮችን በምሳሌነት በመጥቀስ መፍትሔውን አብራሩ ።

- ❖ **በዛሬው ምንባብ በመወያያ ጥያቄዎቹ ያልተዳሰሰ ሀሳብ ካለ በቀራችሁ ጊዜ ተወያዩበት ።**

### ማጠቃለያ

የእግዚአብሔር ልጅ ጌታ ኢየሱስ የመጣው እውነተኛም የሆነውን አምላክ እንድናውቅ ማስተዋል ሰጥቶናል ። ኢየሱስ ክርስቶስ እውነተኛ አምላክና የዘላለም ሕይወት ነው ። በዚህ ዘመን የምንገኝ አማኞች እንደ እስራኤላዊያን ጣኦታትን ገንብተን ባንሰግድም በጓዳዎቻችን ውስጥ በእኛ እና በእግዚአብሔር መሃል ጣልቃ ገብተው የቆሙ መልኮቻቸውን የቀየሩ ብዙ ጣኦታት ሊኖሩ ይችላሉ ። ማናቸውም መልካም የሆኑ በራሳቸው ኃጢአት ያልሆኑና ለሕይወታችን ጠቃሚ የሆኑ ነገሮች እንኳ ቢሆኑ ከእግዚአብሔር ካስበለጥናቸው እንደ ጣኦት ሊሆኑብን ይችላሉ ። ለምሳሌ: ገንዘብ ፣ ስልጣን ፣ ዘር ፣ ትምህርት ውበት ወዘተ መጥቀስ ይቻላል ። ስለዚህ በቤታችን ውስጥ ያሉትን ከእግዚአብሔር ሃሳብና ፍቃድ ሊለዩን ያሉትን ነገሮች አውጥተን እንድንጥል እግዚአብሔር ጸጋውን ያብዛልን ።

**በቃል የሚጠና**

“የዘላለም ሕይወት እንዳላችሁ ታውቁ ዘንድ በእግዚአብሔር ልጅ ስም ለምታምኑ ይህን ጽፌላችኋለሁ ። ” **1ኛ ዮሐ 5፤13**

“ልጆች ሆይ፥ ከጣዖታት ራሳችሁን ጠብቁ” **1ኛ ዮሐ 5፤21**

## 2.2 የሐዋርያው ዮሐንስ መልዕክት ሁለተኛ

**መግቢያ**

**የመልዕክቱ ዋና ሐሳብ:** በእውነት ጸንቶ መመላለስ

**ታሪካዊ ዳራ**

**የመልዕክቱ ጸሐፊ እና የተጻፈበት ዘመን**

ጸሐፊው ዮሐንስ ሲሆን ራሱን ሽማግሌው በማለት ይገልጻል(ቁ1) ። ይህ የሆነው ከመጀመሪያዎቹ ሐዋርያት መካከል ዮሐንስ ብቻ ዕድሜ ጠግቦ በሕይወት የነበረ አገልጋይ በመሆኑ ነው ። እንደሌሎቹ መልዕክቶች ሁሉ ሁለተኛው የዮሐንስ መልዕክት ከ85-95 ዓ.ም ባለው ጊዜ ውስጥ በኤፌሶን ሳይጻፍ አይቀርም ።

**የመልዕክቱ ተደራሲ**

ዮሐንስ ይህን መልዕክት ለተመረጠችው እመቤትና ለልጆቿ በማለት ነው (ቁ 1) ። አንዳንዶች ለተመረጠችው እመቤት የሚለውን ሐረግ በዘይበአዊ አገላለጽ ለአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ነው ሲሉ ለልጆቿ ሲባል ደግሞ አባላቱን ያመለክታል ይላሉ ። የተመረጠችው የእኅትሽ (ቁ13) የሚለው ሐረግ ደግሞ አሁንም በዘይቤአዊ አገላለጽ እኅት ማኅበረ- ምዕመናንን ያሳያል በማለት ይተረጉሙታል ። ሌሎች ደግሞ መልዕክቱን በእማሬያዊ ትርጉም ረገድ /በቁሙ ወይም በቀጥታ/ በማየት መልዕክቱ የተጻፈላት ሴት ዝነኛ የሆነች በታናሹ እስያ የምትኖር በዮሐንስ ዘንድ የምትታወቅና እርሱ መንፈሳዊ አባትና ባለ ስልጣን በሆነበት በቅርብ አካባቢ ትኖር የነበረች መበለት ናት በማለት የዚህን ሐረግ ምንነት ይተረጉማሉ ።

**ዓላማ**

ዮሐንስ ከሐዋርያዊ ትምህርት ርቀው የስሕተትን ትምህርት የሚያሰራጩትን ተዘዋዋሪ አገልጋዮች /አስተማሪዎች፤ወንጌላውያንና ነቢያት / በእንግድነት ስለ መቀበል፤ ስለ መስጠት ወይም እርዳታ ስለ ማድረግ "የተመረጠችውን እመቤት" ለማስጠንቀቅ ይህን መልዕክት ጻፈ(ቁ 7-8) ። በመሆኑም ዮሐንስ "የተመረጠችውን እመቤት"ና ልጆቿን በእውነት ጸንተው እንዲኖሩ (ቁ4) ያበረታታል ።

## ጥናት 8
## ሽማግሌው
## <u>የምንባብ ክፍል፡ 2ኛ ዮሐ 1-13</u>

**መግቢያ፡** በዛሬው ጥናታችን ሐዋርያው ዮሐንስ ፍቅር በክርስቲያን ህይወት እጅግ አስፈላጊ በመሆኑ ፤ እርስበርሳችን መዋደድ እንዳለብንና፣ የኢየሱስ ክርስቶስን ትምህርት ከማይቀበሉ ሓሰተኛ አስተማሪዎች ጋር መተባበር እንደሌለብን እናያለን ።

### የመወያያ ጥያቄዎች

1. (ቁ 1-3) መልእክቱ ለእነ ማን እንደተጻፈላቸውና የሰላምታውን አሳብ አብራሩ ።
2. (ቁ 4) የመልእክቱን ፀሐፊን ሐዋርያው ዮሐንስን እጅግ ደስ ያሰኘው ምንድር ነው?
3. (ቁ 5) ከመጀመሪያ በእኛ ዘንድ የነበረች ትእዛዝ ናት እንጂ አዲስ ትእዛዝ አይደለም የተባለችው ትእዛዝ የትኛዋ ናት? ሐዋርያው ይህን የመጻፉ አስፈላጊነትስ ምንድር ነው?
4. አሳቾች የተባሉት እነማን ናቸው? ስህተታቸውስ ምን ነበር?
5. በክርስቶስ ትምህርት የማይኖር ሰው ምን ዓይነት ሰው ነው? ከእንዲህ ዓይነቱ ሰው ጋር አማኝ ምን ዓይነት ግንኙነት ሊኖረው ይገባል?

### ከሕይወት ጋር ማዛመድ

6. ለእኛ ለአማኞች እርስ በርሳችን መዋደድ ከመጀመሪያው የተሰጠን ትእዛዝ መሆኑንና፤ በዚህ ትእዛዝ ለመሄድ የእውነትኛ ፍቅር አስፈላጊነት ምን ያህል እንደሆነ ተረድተሃል/ሻል?

- **በዛሬው ምንባብ በመወያያ ጥያቄዎቹ ያልተዳሰሰ ሀሳብ ካለ በቀራችሁ ጊዜ ተወያዩበት ።**

### ማጠቃለያ

የክርስትና ሕይወት ዋነኛዉ መገለጫ እርስ በርሳችን መዋደዳችን ነው ። ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በዮሐንስ ወንጌል 13፥ 35 ላይ “እርስ በርሳችሁ ፍቅር ቢኖራችሁ፥ ደቀ መዛሙርቴ እንደ ሆናችሁ ሰዎች ሁሉ በዚህ ያውቃሉ” ብሏልና እርስ በርሳችን ልንዋደድ ይገባናል ። በአንጻሩም ደግሞ ዛሬም በእኛ ዘመን ብዙ ሐሰተኛ አስተማሪዎች ስላሉ እውነትኛውን የእግዚአብሔር ቃል ዕለት ዕለት በማወቅና በመረዳት ራሳችንንና ወገኖቻችንን ከሐሰተኛ ትምህርት ልንጠብቅ ይገባል።

### በቃል የሚጠና

“እንደ ትእዛዛቱም እንሄድ ዘንድ ይህ ፍቅር ነው፤ ከመጀመሪያ እንደ ሰማችሁ፥ በእርስዋ ትሄዱ ዘንድ ትእዛዙ ይህች ናት ። ብዙ አሳቾች ወደ ዓለም ገብተዋልና እነርሱም ኢየሱስ ክርስቶስ በሥጋ እንደ መጣ የማያምኑ ናቸው፤ ይህ አሳቹና የክርስቶስ ተቃዋሚው ነው። “2ኛ ዮሐ 6-7

## 2,3 የሐዋርያው ዮሐንስ መልዕክት- ሦስተኛ

**መግቢያ**

**የመልዕክቱ ዋና ሐሳብ:** በታማኝነት ማገልገል
**ታሪካዊ ዳራ**
**የመልዕክቱ ጸሐፊ እና የተጻፈበት ዘመን**

ጸሐፊው ዮሐንስ ሲሆን ይህ የተወደደው ሐዋርያ በድጋሚ ራሱን ሽማግሌው በማለት ያስተዋውቃል (ቁ1) ። እንደ ሌሎቹ መልዕክቶች ሁሉ ሦስተውኛው መልዕክትም በሰማኒያዎቹ ዓመታት ማክተሚያ ወይም በዘጠናዎቹ ዓመታት መግቢያ ላይ በኤፌሶን ከተማ ሳይጻፍ አልቀረም ።

**የመልዕክቱ ተደራሲ**

ዮሐንስ ይህን ግላዊ መልዕክት የጻፈው ጋይዮስ ለተባለ ታማኝ ክርስቲያን (ቁ1) ሲሆን ጋይዮስ በታናሹ በሚገኙት ክርስቲያናዊ ማኅበረ ሰቦች ውስጥ አባል ሳይሆን አይቀርም ። በመጀመሪያው ምእተ ዓመት መጨረሻ አካባቢ ከከተማ ወደ ከተማ እየተዘዋወሩ የሚያገለግሉ ወንጌላውያን በቤታቸው ተቀብለው በሚያተናግዷቸውና በጉዟቸው በሚረዷቸው አማኞች ብዙ ጊዜ ድጋፍ ይደረግላቸው ነበር (3ኛ ዮሐ ከ5-8ን እና ሮሜ 16:23)ን አንብቡ ።

**ዓላማ**
ዮሐንስ ይህን መልዕክት የጻፈው ታማኝ የሆኑትን ተዘዋዋሪ አገልጋዮች ጋይዮስ በታማኝነት በመቀበሉና በመርዳቱ እርሱን ለማመስገን(ቁ 3-8 )፤ ዐመጸኛ የሆነውን ዲዮጥራጢስን ግን ለማስጠንቀቅና እንዲሁም ለራሱ ለዮሐንስ የወደፊት የጉብኝት መንገድ ለመጥረግ ነው(ቁ13-14 )።

**ጥናት 9**

**ሽማግሌው**

**<u>የምንባብ ክፍል፡ 3ኛ ዮሐ 1-15</u>**

**መግቢያ፡** ባለፈው ጥናት በ2ኛ የዮሐንስ መልእክት ላይ ፍቅር ለአማኞች እጅግ አስፈላጊ በመሆኑ ፤እርስ በርሳችን መዋደድ እንዳለብንና፣ የኢየሱስ ክርስቶስን ትምህርት ከማይቀበሉ ሓሰተኛ <u>አስተማሪዎች ጋር</u> መተባበር እንደሌለብን ተመልክተን ነበር ። በዛሬው ጥናታችን ደግሞ፤ ከስፍራ ስፍራ የሚዘዋወሩ ክርስቲያን የወንጌል አገልጋዮችን በምንችለው ሁሉ መደገፍና መርዳት እንዳለብን እናያለን ።

**የመወያያ ጥያቄዎች**

1. (ቁ 1-4) ሐዋርያው ዮሐንስ ለጋይዮስ እጸልያለሁ ያለው የጸሎት ርዕሶችን ምን ምን ናቸው? ሐዋርያውንስ ያስደሰተው ነገር ምን እንደሆነ በዝርዝር ግለፅ ።
2. (ቁ 5-8) ጋይዮስ የተመሰገነው ምን ስላደረገ ነው? በእንግድነት የተቀበለውስ እነ ማንን ወይም ምን አይነት ሰዎችን ነበር ?
3. 3. (ቁ 9-10) ሐዋርያው ዮሐንስ ዲዮጥራጢስን የወቀሰባችው ነገሮችን በዝርዝር ግለፅ።
4. (ቁ 11) ሐዋርያው ፣ ጋይዮስን ምን እንዲመስል ነው የሚመክረው? ለምን?
5. (ቁ 12) ለድሜጥሮስ የሚመሰክሩ እነማን ናቸው? ስለ ምስክርነታቸውስ እውነትነት ምን እናውቃለን ።

**ከሕይወት ጋር ማዛመድ**

6. በግልህ/ሽ ወንገልን ለማዳረስ ምን ያህል እየተጋህ/ሽ ትገኛለህ/ሽ ? ለወንጌል አገልግሎት በየዓለማቱ በትክክል የሚደክሙትንስ እግዚአብሔር በሰጠህ/ሽ አቅም ለመደገፍ ምን ያህል ፈቃደኛ ነህ/ሽ ? በምን በምን መደገፍ እንደሚቻል ተሞክሮአችሁን ለቡድናችሁ አጋሩ ።

- **በዛሬው ምንባብ በመወያያ ጥያቄዎቹ ያልተዳሰሰ ሀሳብ ካለ በቀራችሁ ጊዜ ተወያዩበት ።**

**ማጠቃለያ**

ሐዋርያው ዮሐንስ ለወዳጁ ለጋይዮስ ጤና እና ሁለንተናዊ መከናወን እንደጸለየ ሁሉ፣ እኛም እንዲሁ እርስ በርሳችን ዘወትር በጸሎት እየተሳሰብን እና በእውነት ጌታን እየተከተልን በወንጌል ሥራ የሚደክሙትን ልንቀበልቸው እና ልንደግፋቸው ይገባናል ።

**በቃል የሚጠና**

“ ወዳጅ ሆይ፥ ነፍስህ እንደሚከናወን፥ በነገር ሁሉ እንዲከናወንልህና ጤና እንዲኖርህ እጸልያለሁ።”
3ኛ ዮሐ 2

# ክፍል ሦስት

## የያዕቆብ ወንድም የይሁዳ

## <u>መልዕክት</u>

# የያዕቆብ ወንድም የይሁዳ መልዕክት

**የመልዕክቱ ዋና ሐሳብ:** ለእምነት ተጋድሎ ማድረግ

## ታሪካዊ ዳራ

### የመልዕክቱ ጸሐፊ እና የተጻፈበት ዘመን

ጸሐፊው ይሁዳ ሲሆን "የያዕቆብ ወንድም" እንደሆነ በመግለጽ ራሱን ያስተዋውቃል (ቁ 1) ። በአዲስ ኪዳን ውስጥ የኢየሱስ ወንድሞች ተብለው የተጠሩት ይሁዳና ያዕቆብ ብቻ ናቸው። (ማቴ13:55 ማር6:3) ። ያዕቆብ በኢየሩሳሌም በነበረችው ቤተ ክርስቲያን በመሪዎቹ ታዋቂ ስለ ነበር ይሁዳ የእርሱ ወንድም መሆኑን መጠቆም የፈለገው የራሱን ማንነት ለመግለጽ ይሆናል ። መልዕክቱ የተጻፈበት ዘመን ከ70 -80 ዓ.ም ባለው ጊዜ ውስጥ እንደሆነ ይታመናል ።

### የመልዕክቱ ተደራሲያን

ይህ አጭር ነገር ግን ጠንካራ መልዕክት የተጻፈው በጸጋ ድነናልና ኃጢአት ብሰራም አይፈረድብንም ብለው በድፍረት የሚያስተምሩትን እንዲሁም ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ ብሕርይና ሰው መሆን አስቀድሞ በሐዋርያት የተነገረውን መገለጥ አጥብቀው የሚክዱትን (ቁ4) የሐሰት አስተማሪዎችን በመቃወም ሲሆን የመልዕክቱ ተደራሲያን በግልጽ አልተጠቀሱም ። ምናልንባት በሁለተኛ ጴጥሮስ የተጠቀሱት ተደራሲያን ራሳቸው ሊሆኑ ይችላሉ ። (የሁለተኛ ጴጥሮስን መግቢያ ይመልከቱ) ።

### ዓላማ

ይሁዳ ይህን መልዕክት  የጻፈው (1) ስለ ሐሰተኛ አስተማሪዎች አደገኛ አካሄድና በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ሰለሚያደርጉት አፍራሽ እንቅስቃሴ አማኞች ፈጥነውብ፟እንዲያውቁት ለማድረግ እንዲሁም (2)እውነተኛ አማኞች እንዲነሱና ለቅዱሳን አንዴና ለመጨረሻ ስለ ተሰጠው እምነት እንዲጋደሉ (ቁ3) ለማበረታታት ነው ።

**ጥናት 1**

**ዐመጸኞች የሚጠብቃቸው ፍርድ**

**<u>የምንባብ ክፍል፡ የይሁዳ መልዕክት ከቁ.1-16</u>**

**መግቢያ፡-** በዛሬው ጥናት ክርስቲያኖች ለእምነታቸው እንደሚገባው እንዲጋደሉ እየመከረ በእግዚአብሔር እውነት ላይ የሚነሱ ዐመጸኞች እጅግ በክፋት የተሞሉ ቢሆኑም ከፍርድ እንደማያመልጡ ሲያሳስብ እንመለከታለን።

**<u>የመወያያ ጥያቄዎች</u>**

1. ከቁ1-3 ይሁዳ ስለምንካፈለው ድነት ልጽፍላችሁ እጅግ ጓጉቼ ነበር ሆኖም ስለእምነታችሁ እንድትጋደሉ ለመምከር እጽፍላችኋለሁ ማለቱ ድነታችንን በእምነት መጠበቅ ምን ያህል አስፈላጊ እንደሆነ ያሳይሃል?
2. በቁ4 በመጀመሪያይቱ ቤተክርስቲያን የአምላካችንን ፀጋ በሴሰኝነት የሚለውጡና የጌታችንን የኢየሱስ ክርስቶስ ጌትነት የሚክዱ ሾልከው ከገቡ በመጨረሻው ዘመን ባላቸው በአሁኗ ቤተክርስቲያን እንዴት የከፋ ሊሆን እንደሚችል ተወያዩበት።
3. በቁ5 እግዚአብሔር መሃሪና ተስፋውን ጠባቂ አምላክ ከመሆኑ የተነሳ ከግብጽ ባርነት ያወጣቸውን ከሃጢያታቸውና ካለማመናቸው የተነሳ በምድረ በዳ ሲጠፉ እንዳልራራላቸው ሁሉ እግዚአብሔር ይቅር ባይ ብቻ ሳይሆን የተስፋውን ቃል የሚንቁትን እንደሚገስጽ በመዘርዘር አስረዱ።
4. በቁ 6 የእግዚአብሔርን ክብር በተገዳዳሩ በእርሱ ላይ በአመጽ የተነሱትን መላዕክት እንኳን ሳይምር ወደ ምድር መጣሉን ስታይ እግዚአብሔር ፃድቅና ቅዱስ መሆኑን እንዴት እንደሚያሳይ ግለጽ።
5. ከቁ 7-8 እግዚአብሔር በሰዶምና ጎሞራ በዙሪያቸው የነበሩትን ከተሞች በእሳትና በድኝ ያጠፋው ምን አይነት ሰዎች ስለነበሩ ነው? ይሁዳ ይህንን ሲያነሳ ምን ምን ለማስተማር ፈልጎ ነው?
6. ከቁ9-13 በእግዚአብሔር እውነት ላይ በስድብና በዐመጽ የተነሱትን ሰዎች በቃየል መንገድ የሄዱ በበለአም ስህተት ውስጥ የወደቁ በቆሬም መቃወም ጠፍተዋል እያለ የሚገልፃቸው ምን አይነት ባህሪያት እንዳላቸው ለማሳየት እንደፈለገ አስረዳ ። /ዘፍ 4÷3፣ 2ኛ ጴጥ 2÷15 ፣ ዘሁ 16÷1-7/

- **በዛሬው ምንባብ በመወያያ ጥያቄዎቹ ያልተዳሰሰ ሀሳብ ካለ በቀራችሁ ጊዜ ተወያዩበት ።**

**ከሕይወት ጋር ማዛመድ**

**7.** ከተፈጥሮ ስርዓት ውጪ በገዛ ምኞታቸው የሚሄዱና ነውራቸው ክብራቸው የሆነባቸው ሰዎች ቃሉን ከራሳቸው ስሜት ጋር ሲያጣምሙ ይህንን ለመከለከል በዚህ ዘመን ምን ዓይነት ጥንቃቄ ልናደርግ ይገባል ይመስላችኋል?

**ማጠቃለያ**

እግዚአብሔር ቸር፣ ሩህሩህና ይቅር ባይ አምላክ እንደሆነ ሁሉ ሃጢአትንና አመጽን ነውርንም ሁሉ የሚጠላ አምላክ መሆኑን ልንረሳ አይገባንም ። ምንም ያህል ትዕግስቱና ፍቅሩ ሰፊ ቢሆንም ፍርዱም የጽድቅና አሰራሩም የማይመረመር መሆኑን እናስተውል ።

**በቃል የሚጠና**

"የመላዕክት አለቃ ሚካኤል ግን ከዲያብሎስ ጋር በተከራከረ ጊዜ ስለ ሙሴ ስጋ ሲነጋገር ጌታ ይገስጽህ አለው እንጂ የስድብን ፍርድ ሊናገረው አልደፈረም ።" ይሁዳ 9

## ጥናት 2

## በእምነት መጽናት

## የምንባብ ክፍል፡ የይሁዳ መልዕክት ከቁ.17-25

**መግቢያ፡-** ባለፈው ጥናት ክርስቲያኖች ለእምነታቸው እንደሚገባው እንዲጋደሉ እየመከረ በእግዚአብሔር እውነት ላይ የሚነሱ ዐመጸኞች እጀግ በክፋት የተሞሉ ቢሆኑም ከፍርድ እንደማያመልጡ ሲያሳስብ ተመልክተን ነበር ። በዛሬው ጥናታችን ደግሞ ምኞታቸውን ከሚከተሉ አሳቾች ለመጠበቅ አማኝ በእምነት ፀንቶ እንዲቆም ቅዱስ ቃሉን ማጥናትና በፀሎት ሊተጋ እንደሚገባ ሲያሳስብን እንመለከታለን ።

**የመወያያ ጥያቄዎች**

1. **ከ**ቁ17-18 በመመልከት ስለ ሁሰተኛ አስተማሪዎችና አስተምህሮቸው በቃሉ የተሰጠንን ማስጠንቀቂያ አስተውለን በየትኛውም ቦታና ጊዜ የምንሰማውን ቃል በቅዱስ ቃሉ መፈተሽ ለምን ይጠቅመናል ።
2. በቁ.19 እነዚህን የሚያለያዩ ስጋውያንን የሆኑ መንፈስም የሌላቸው ሰዎች ናቸው ሲል ምን ማለቱ እንደሆነና ስጋዊነት በክርስትና ህይወት እንዴት እንደሚገለጽ ተወያዮበት ።
3. በቁ.20 የእግዚአብሔርን ቅዱስ ቃል በማጥናትና በፀሎት ራሳችንን ማነጽ በየጊዜው ከሚመጡ ሀሰተኛ ትምህርቶች እንዴት ሊጠብቀን እንደሚችል አስረዳ ።
4. **ከ**ቁ.21-23 በጊዜውም ያለጊዜውም ፀንተን እንድንቆም ብቻ ሳይሆን ሌሎችም እንዲጠነክሩና ከሀሰተኞችም እንዲጠበቁ በግልና እንደ ቤተክርስቲያንም ምን ማድረግ እንደሚገባን ያለንን ድርሻ ተወያዩበት ።
5. **ከ**ቁ.24-25 ፀንተን እንድንቆም እግዚአብሔር በድካማችን በጉድለታችን ረድኤታችንና መሆኑን ማወቃችን በእርሱ ሁሉን ቻይነት ተደግፈን እንድንኖር እንዴት ሊያግዘን ይችላል ?

**ከሕይወት ጋር ማዛመድ**

6. በዚህ ዘመን ቃሉን የሚያውቁትን እየተሳደቡ ካለ ሀፍረት የእግዚአብሔርን ቃል እያቃለሉ የሚዘብቱ አስተማሪዎች እንዴት ብዙዎችን እንደሚያስቱና ብዙዎችም እንደሚስቱ ተወያዩበት ።

- **በዛሬው ምንባብ በመወያያ ጥያቄዎቹ ያልተዳሰሰ ሀሳብ ካለ በቀራችሁ ጊዜ ተወያዩበት ።**

**ማጠቃለያ**

በክርስትና ህይወት ጉዞ ብዙ ተግዳሮት የሚያጋጥም ሲሆን አማኝ በተመሰረተበት እውነት ፀንቶ እንዲቆም የሚያስችለውን ቅዱስ ቃሉን በየእለቱ እንዲያጠናና በፀሎት እንዲተጋ ይገባዋል ።

**በቃል የሚጠና**

" እናንተ ግን ወዳጆች ሆይ ከሁሉ ይልቅ በተቀደሰ ሀይማኖታችሁራሳችሁን ለማነጽ እየተጋችሁ በመንፈስ ቅዱስ ፀልዮ ። " **ይሁዳ 20**